# የዲሬክተሮች፡ቦርድ

**አበራ፡ፍርዴ**
ኪዳ፡መንበር
**ያዕቆብ፡ሀይለማርያም**
**ፈንታሁን፡ጥሩነህ**
**አህመድ፡ኑር**

**ዋና፡አዘጋጅ**
ፈንታሁን፡ጥሩነህ

**የአዘጋጅ፡ቦርድ**
ሠይፉ፡በካይ
አበሳብዋ፡ተሰፋዬ

**የስርጭት፡ሀላፊ**
አህመድ፡ኑር

**የአማካሪ፡ቦርድ**
ክፍአለ፡ገብረ፡ጊዮርጊስ
ማይገነት፡ሽፈራው
(ሜሪላንድ፡ሰሜን፡አሜሪካ)

ጌትነት፡በካይ
(በርሊን፡ምዕ.ጀርመን)
አንዩ፡ቦናና
(ማኪያን)
ጸሐፊዎችን፡በዚህ፡አድራሻ፡መላክ፡ይቻላል።

From the Library of
ፍስሃ አጥላው ወልደ ዮሐንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

**SEM INNA WORQ**

**P. O. BOX 43003**

**WASHINGTON, D.C. 20010**

**U.S.A.**

ISSN: 0891-9119

Sem Inna Worq Corporation is a non-profit, tax-exempt organization. Washington, D.C. U.S.A.

# ማውጫ


፩. ርዕሰ አንቀጽ 1

፪. ደብዳቤዎች 9

፫. የብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ የሕይወት ታሪክ 21

፬. ኢትዮጵያ የሚለው ቃል እውነተኛ ትርጉም 36
ገ/ኢ ኅርፋ፣ ከሎስ አንጀለስ

፭. የምርምር ሠነዶች፣ ጥያቄዎች፣ ማስታወሻዎች 41

፮. እዋልዶ-ወንጄ 56
ገ. ኑ. ብልማርር፣ ከስዊድን

፯. የደረሱን መፃሕፍት፣ መጽሔቶችና ጋዜጦች 72

፰. የደረሱን የፖለቲክ ጽሑፎች 76

፱. ነፃ መጽሔቶችና ጋዜጦች 84

፲. ቅኔ 87
Mr. Pen፣ ከኒውጀርሲ

፲፩. የቃላት ፍች 89

# ርዕሰ አንቀጽ

## ስለ ኢትዮጵያ የሚደረጉ ጉባኤዎች አቅጣጫ

በኢትዮጵያ የጉባኤ ባህል ከጥንት ጀምሮ የቆየ ነው። ሊቃውንት በተለያየ ጊዜና በተለያየ ርዕስ ላይ ለመነጋገር የሚጠቀሙበት መሰርያ እንደነበር የታሪክ ምዕራፎች ይናገራሉ። አብዛኛውን ጊዜ በቤተክህነት ሊቃውንት መከከል ጉባኤ የማድረግ ባህልና ልምድ እንደነበር ሲታወቅ የዚህ ባህል ሂደትና ውድቀት ከዚሁ ተቋም ጋር በየወቅቱ ብቅ እያለ ሲጠፋ ኖሩዋል። ስለዚህም በቤተክህነት አከባቢ የሚነሡ ክርክሮችና ቅራኔዎች አልባት የሚያገኙት በጉባኤ ሰቢያ ነበር። ይህ ሲባል ግን ከሀይማኖት ውጭ ጉባኤ ግብር ላይ አልዋለም ለማለት አይደለም። አስተዳደራዊ ችግርና የፀጥታ መታወክ በሚደርስበት ጊዜ ሁሉ በመንግስት ደረጃ ጉባኤ ይደረጋል፣ መፍትሔም ይዘየዳል።

በኢትዮጵያ ውስጥ የጥናት ጉባኤዎች መቼ እንደተደረጉ በምንጠይቅበት ጊዜ አጥጋቢ መልስ ማግኘት አዳጋች ነው። በተለይ አንድን የፖለቲክ አስተዳደር፣ የሕብረተሰብን፣ የሥነ-እአምሮን፣ የቤተሰብን፣...ችግር መነሻና መድረሻውን አጥንቶ መፍትሄ ለመሻት ጉባኤ የተከሄደበትና ሕዝብ የተሰተፈበትን ጊዜ ብንቆጥር እጅግ ኢምንት ሆኖ እናገኘዋለን። በተለይም ሀገሪቱ ከተጋፈጣት የችግር ብዛት ትይዩ ሲታይ በኢትዮጵያውያን የተከሄደው የጥናት ጉባኤ ቁጥር እጅግም ነው። በንፃሩ የውጭ ሀገር ተመራማሪዎች ስለ ኢትዮጵያ ያደረጉት የጥናት ጉባኤ በጣም ጎልቶ ይታያል።

ኢትዮጵያ የታሪክ ጎተራ እንደመሆንዋ መጠን የተለያዩ የአውሮፖ ሊቃውንት ይህን የረጅም ዘመን ታሪክ ዲካ ለማግኘት አያሌ የጥናት ሥምሪት አድርገዋል። ይህ የጥናት ሥምሪት የሰስት መቶ ዓመት ዕድሜ አለው። በኢትዮጵያ ላይ ያተከረ ጥናት የተጀመረው ሉዶልፍ (1652- 1704 እ.ኤ.አ) በተባለው ጀርመናዊ

ነበር። ሉዶልፍ ከአባ ጎርጎሪዮስ ጋር ለአሥር ዓመታት ያህል የጥናት ጓደኝነት ነበረው። ከ300 ዓመታት ያህል በኋላ ደግሞ ፕሮፌሰር ሚትዎችና አለቃ ታየ በኢትዮጵያ ጥናት ተግበር ላይ ተበብረዋል። ከነዚህ ጀመራዎች በኋላ ግለሰብ ተመራማሪዎች በተለያዩ ሀገሮች ስለ ኢትዮጵያ ማጥናታቸውን ቀጥለዋል። ለምሳሌ ለመጥቀስ ዋልስ በጅ በእንግሊዝ ሀገር፣ ኢኖ ሊትማን በጀርመን፣ ከንቲ ሮሲኒ በጣሊያን፣ ማሪሴ ኮኸን በፈረንሳይ፣ ቱረየቭ በሩሲያ፣ ወልፍ ሌስለው በአሜሪካ።

በውጭ ሀገሮች ስለ ኢትዮጵያ የተደረጉ ጥናቶች ከግለሰቦች አልፎ ዓለም አቀፍ መልክ ይዞ በጉባኤ ደረጃ እየተከሄደ እስከለንበት ዘመን ደርሷል። እስከሁን አሥር የሚሆኑ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎች ተከሂደዋል። የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ ጉባኤ በሮማ ከተማ በ1951 ዓ/ም ተከሄደ። ሁለተኛው ጉባኤ በ1955 ዓ/ም በእንግሊዝ ሀገር ተደረገ። ሦስተኛው ጉባኤ በ1958 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ፣ አራተኛው ጉባኤ እንደገና በሮማ ከተማ በ1965 ዓ/ም፣ አምስተኛው በፈረንሳይ ሀገር ኒች ከተማ በ1970 ዓ/ም፣ ስድስተኛው እስራኤል ሀገር በ1973 ዓ/ም፣ ሰበተኛው ስዊድን ሀገር በ1975 ዓ/ም፣ ስምንተኛው አዲስ አበባ 1977 ዓ/ም። በነዚህ ጉባኤዎች ላይ የኢትዮጵያዊያን ተሰትፎ እጅግ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ማወቅ ተችሏል። አዲስ አበባ ላይ በተደረገው ጉባኤ ጊዜ የኢትዮጵያውያን ተሰትፎ ጎላ ብሎ ታይቶ ነበር። ጽሑፍ አቅርበው የታተመላቸው ኢትዮጵያን አስራ ስምንት ይሆናሉ። ከዚህ ጉባኤ በቀር በሌሎች ዓለም አቀፍ ጉባኤዎች የተሰተፉ ኢትዮጵያውያን ቁጥር በውክልና ደረጃ አጥጋቢ ነው የሚባል አይደለም። ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ ጠይቆና ተመራምሮ መልስ ማግኘት ወደፊት ለሚደረጉ ጉባኤዎችና አሁን በመደረግ ላይ ላሉ ጉባኤዎች አርምጃ አያሌ ጥቅም አለው። አብሮም መጠናት ያለበት ነገር የውጭ ምሁራን ለምን ኢትዮጵያን ለማጥናት ጉባኤ መጥራት ደረጃ ደረሱ የሚለው ጥያቄ ነው።

ያም ሆነ ይህ ኢትዮጵያውያን ስለሀገራችን ለማጥናትና

ችግሮችን ለመፍታት ጉባኤዎች በመጥራት በመወያየት ራሳችንን መቻል እንዳለብን ማንም ሊነግረን የሚችል ጉዳይ አይደለም። በባህላችን ደም ስር የተዋሀደ ሆኖ ሳለ በታሪክ ሂደት ምክንያት ተቋርጦ የቀረውን ባህል እንስቶ መጠቀም የኛ ፈንታ ነው። በተለይም ባለንበት ዘመን በሀገሪቱ ውስጥ አያሌ ውስብስብ ችግሮችን በመከራከርና በጥናት ላይ የተመሰረቱ ዘዴዎች በመፈለግ ለማስወገድ ጥድፊያ በሚያስፈልግበት ጊዜ በኢትዮጵያውያን በራሳቸው የሚከሄዱ የጥናት ጉባኤዎች አይነተኛ መፍትሄ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ መረዳት ጠቃሚ ነው። የምልዐተ ሕዝቡን ድምጽ፣ ሀሳብ፣ ዝንባሌ፣ ምኞት፣ ፍላጎትና የመሳሰሉትን ሁሉ ማወቅ የሚቻለው ሀሳብ ለሀሳብ መገበያያ መድረክ ሲኖር ነው። የጥናት ጉባኤዎች በተለይ እነዚህን ስለሕዝብ የሚደረጉ ጥናቶችን አቀናብሮ እና አሳጥሮ ማቅረብ ያስችላሉ። በጉባኤ ወቅት ትችት መለዋወጥ፣ ጥያቄ መጠየቅ፣ ቅራኔዎችን ማለዘብ ብሎም መፍታት ይቻላል። አንዱ ያወቀውን ለሌላው ያሳውቃል፣ የተለያዩ ሀሳቦች ተፋጭተው መስከን ይችላሉ፤ በዚህ ግንኙነት ወቅት ሀሳቡ ጠባብነትና የእኔ ብቻ አዋቂነት አስተሳሰብ በሀሳቡ ሰፊነትና በህዝብ ድምጽ መመከት እንዲሁም የሌላውን በማክበር አስተሳሰብ እየተለወጠ ይመጣል። በጉባኤዎች ወቅት የሚቀርቡ የጥናት ርዕሶች በሚብራሩበት ጊዜ የሰዎች ግንኙነት አብሮ የማደግና የመዳበር አቋም እየተከለ ይሄዳል። ይህን ዓይነት ጥቅም ለመቀዳጀት ነፃ የሆነ መድረክ እጅግ ያሻል። አለበለዚያ ጉባኤዎች ለእሉታዊ ተግባር መዋል ይጀምራሉ፣ ይቀጥላሉም። ጉባኤዎች የመታዘቢያ እና የስለላ መድረክ መሆን ይችላሉ ለማለት ነው። እነዚህን ዓይነት ድክመቶች የሚያዘምት ሥርዓት ሆኑ ብሎ አሸንጉሊት ሸንጎዎችና ጉባኤዎች በመቋቋም የተቀናቃኞችን ሀሳብና አዝማሚያ መሰለያ መድረክ ሊያደርገው ይችላል። በተጨማሪም የተቀናቃኝን ወገን ቅስም ለመስበርና ለማጥቃት መድረክ መሆን ይችላል። ይህ በፖለቲካው ሥርዓትና በሕዝቡ የዕድገት ፍላጎት መካከል ያለውን ቅራኔ አመልካች ነው። ይህ ዓይነት እሉታዊ ድርጊት በአለፈው ስርዐት የፖርለማ ጉባኤዎች እንዲሁም በአዲሱ ሥርዓት የውይይት ክበቦች መካሄዱን ማስታወስ ትምህርታዊ ይሆናል። ይህ ድርጊት በሌሎች

የፖለቲካ ድርጅቶችም እንደሚከሄዱ መጠቆም ተገቢ ይመስለናል። እነዚህ በሁሉም አቅጣጫ ሥር ሰደው የሚገኙ አሉታዊ ተግባሮች የሚመነጩበትን አከባቢና ምክንያት መፈለግ በጉባኤዎች ሰቢያ የሚደረጉትን አሉታዊ ተግባሮች ከማስወገዱ በለይ በጉባኤዎቹ ወቅት የሚፈጠሩ አለስፈለጊ ጭንቀቶችና ውጥረቶችን ያለለል። ጤናማ ጉባኤዎች በነፃ መንፈስ እንዲከሄዱ በር ከፋች እርምጃ ነው እንለለን።

ጠባብ የቡድነኝነት ስሜት ለጉባኤዎች አደገኛነት አንድ አቢይ ምክንያት ነው። ሀሰበ ጠባብነት ሌለው አቢይ ምክንያት ሲሆን ውድድርን፣ ጏደኝነትን፣ ጠለትነትን፣ ሀሰብ መግለጽን፣ ሀሰብ መቀበልን፤ ሂስና ትችትን፣ ግለሰብና ምልዐተ ሕዝብን፣ ሰለም ፈለጊነትን የመሰሰሉትን ሁሉ የምናይበት ዘዴና የምንስጠው ትርጉም ተጨማሪ ምክኒያቶች ናቸው ። ጠባብ የቡድነኝነት ስሜት የሚያጠቃው ግለሰብም ሆነ ቡድን በጉባኤ ወቅት ማየት የሚፈልገው የራሱ ቡድን ማቸነፉን፣ የበለይ መሆኑን እንጂ እውነቱን አይደለም። በሀይል ተጠቅሞም ሆነ በነገር ተናድፎ የቡድኑ አስተሰሰብና ሀሰብ የበለይ እንዲሆን ይሟሟታል። በዚህን ጊዜ እውነት ፈለጊዎች ምን ያክል ተሰፋ መቁረጥ እንደሚደርስበቸው ማየት አዳጋች አይደለም። ከግለሰቡ ጥቅም ሌለ፣ ከቡድኑ አሸናፊነት ማዶ፣ ሌለ ሰፊ ሕዝብ መኖሩን በመዘንጋት ጊዜያዊ ግለዊም ሆነ ቡድናዊ ጥቅም በማስቀደም የረጂሙን ጊዜ ሕዝባዊ ሕይወት በመርሰት ጉባኤዎችን ማስጨነቅና ተሰታፊዎችን ማሰደድ ከሀሰብ ጠባብነት የሚመነጭ ድክመት ነው። የአስተሰሰብ ጥበት አብዛኛውን ጊዜ የሚመነጨው ጊዜ ወስዶ ግለሰቡ ራሱን ለመመርመር፣ ለመጠየቅና ግለዊ አቋሙን ለመወሰን፣ ነገሮችን አስፍቶ ለመመልከት ጥረት ለማድረግ ከለመሞከር ነው። ቀለሉ መንገድ አንድ መሪ ወይም ሀይለኛ ተናጋሪ የሚለውን መንገድ መከተል ስለሆነ፣ ያለ ሂስና ያለትችት ያለጥርጣሬ እምኖ በመቀበል ያን ማስተጋበት ነው።

ይህ የሀሰብ ጠባብነት አንድ ገጽታ ነው። የሌለውን ሀሰብ ያለ

አግባብ መገፍተር የሚመጣውና ጉባኤዎችን የሚያደፈርሰው ይህ ዓይነት አክል ነው። ግለሰቡን ሀሰቡ ጠባብ የሚያሰኘው ሌላው ምክኒያት የቡድን ( ድርጅት) መሪዎች ግለሰቦች መሆናቸውን ከመርሳት ወይም የሀሳብ ተመጽዋች አድርጎ እራስን ከማሰለፍ ጋር የሚያያዝ ድክመት ስለሆነ ነው። ይህ ማለት ግን ግለሰቡ ከማንም ጋር አልስማማም ብሎ፣ በሩን ቆልፎ ይቀመጥ ወይም በሌሎች ላይ ያኩርፍ ለማለት አይደለም። ከሌሎች ጋር ለመስማማት ላለመስማማት፣ የተፈጠሩ ቅራኔዎችን ለማለዘብና፣ ለተፈጠሩ ችግሮችና ጥያቄዎች መፍትሄ ለማግኘት እያንዳንዱ ግለሰብ ሀሳቡ ሰፊ አመለካከትና አስተሳሰብ ማዳበር እንዳለበት ማሳሰቢያ ለማስተላለፍ ያህል ነው። ይህ ለውስጠ ድርጅታዊ ጉባኤ ጤና እና መሰከት ጠቃሚ መንገድ ይመስለናል።

ወደተማሪዎች እንቅስቃሴ ታሪክ ገባ ብለን የጉባኤ ባህላቸውን ስንመለከት ትምህርታዊ የሆነ ምሳሌ እናገኛለን። ይህን ተመክሮ ጠቃሚ የሚያደርገው ከመንግሥት ነፃ በመሆን ተማሪዎች ረዘም ላለ ጊዜ ጉባኤዎችን በተከታታይ ማከሄድ መቻላቸው ነበር። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በሀገሪቱ ውስጥ ተማሪዎች እንደ ፖለቲካ ቡድን ራሳቸውን በማሰለፍ የመንግስትን ፖለቲካዊ አቋም በግልጽ መቃወም በጀመሩበት ጊዜ በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚከሄዱ ጉባኤዎች እንዳይቀጥሉ ማዕከላዊ መንግስት ተጽእኖ ማድረግ ጀመረ። አገር አቀፍ የተማሪዎች ማህበር በሀገሪቱ ውስጥ ከስድስት ዓመታዊ ጉባኤዎች በላይ ማድረግ አልቻለም። ኋላም በአዲስ አበባ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበር ( ኡዝዋ) በየግዜው የሚደረገው ንዑስ ጉባኤ ተመሳሳይ እድል ስለአጋጠመው የሕቡና ጊዜው ሲያመች ግልጽ ጉባኤዎች በማፈራረቅ መጠቀም ነበረበት። በሀገሪቱ ውስጥ የጉባኤው ሂደት ሲቋረጥ በውጭ ሀገር ያሉ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ይበልጥ እየተጠናከሩ ዓመታዊ ጉባኤዎችን ሳያቋርጡ ማከሄድ ቀጥለዋል። በዚህም የአውሮፖ ተማሪዎች ማህበር ከአሥራ አምስት ዓመታት በላይ የጉባኤ ልምድ ሲኖረው የሰሜን አሜሪከው ማህበር እስከ ሀያ የሚደርሱ ዓመታዊ ጉባኤዎችን አከሂዷል። የዚህ ልምድ ትምህርታዊነትና ጠቃሚነት

አሊ የሚባል አይደለም። ጉልቶ ይታይ የነበረው የጊዜው የፖለቲካ ችግር አልበት እስከሚያገኝ ድረስ በሀገር ውስጥ ጉባኤ ማካሄድ ባልተቻለበት ሁኔታ በውጭ ሀገር ያሉ የተማሪ ማህበሮች ሀለፊነቱን ወስደው ፖለቲካዊ ጉባኤዎች ማካሄድ፣ ፖለቲካዊ ውሳኔዎችን በየዓመቱ ማስተላለፍ ነበረባቸው። በዚህ ጠባዩ የተማሪዎች እንቅስቃሴ በስደት ላይ ያለ ተቃዋሚ ድርጅት መልክ ነበረው።

አሁን በያዝነው ዘመን የተማሪ ማህበሮች ለፖለቲካ ድርጅቶች መነሻ ከሆኑ በኋላ ሚናቸው የከሰመበት ሁኔታ ይታያል።

ሆኖም ግን አሁንም ቢሆን በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች በሀገሪቱ ማዕከላዊ ፖለቲካ ተወክለው ባለመገኘታቸው ዓመታዊ ጉባኤ አድርገው ውጤቱ የሚገለጸው በሚበትን ወረቀት ላይ ነው። የህዝብን ተሳትፎ ያላገኘ ጉባኤ ምን ያህል እንደሚያጎድል አጠያያቂ አይመስለንም። በማዕከላዊው መንግሥት የሚካሄዱ ጉባኤዎች እምብዛም የሕዝብ ተሳትፎ የአለባቸው አይደሉም። ሕዝብ ማለት ተቃዋሚ ወገኖችንም ስለሚጨምር በማዕከል ደረጃ የሚካሄዱ ጉባኤዎች አንድ ወገነኛና ቡድናዊ (ከልልተኛ) ተጽዕኖ ያለባቸው ጉባኤዎች ከመሆን አያልፉም። አዎንታዊ እርምጃዎች ናቸው ከሚባሉት መካከል አንዳንድ ጥናታዊ ጉባኤዎች በሀገሪቱ ውስጥ የሚያደርጉት እስተዋጽዖ ነው። ይህ እርምጃ ሊበረታታና ሊጎለምስ ይገባዋል። ፖልቲካን አስመልክቶ የሚደረጉ ጉባኤዎች ጠባይ ግን አሁንም ከልልተኛና ቡድናዊ መሆናቸው በገሀድ የሚታይ ነው ። ተቃዋሚ ወገኖች በውጭ ሀገሮች የሚያደርጓቸው ጉባኤዎች ምስክሮች ናቸው። ኢትዮጵያን የሚመለከቱ ጥናታዊ የፖለቲካ ጉባኤዎች ይበልጥ በነፃ መድረክ የሚካሄዱት በውጭ ሀገር ነው። ኢትዮጵያዊያን ስለሀገራቸው የፖለቲካ ዕድል ለመወሰን የሚያደርጉት ጉባኤ አብዛኛው ከሀገር ውጭ መሆኑ ጤነኛ ምልክት አይደለም። እነዚህ ጉባኤዎች በስደት ላይ መሆናቸው ቀደም ሲል በነበረው የፖለቲካ ሥርዓት ምክንያት የተማሪ ማህበራት የፖለቲካ ድርጅትነት ጠባይ እንዲይዙ ከገፋቸው ምክንያት የሚለይ አይደለም።በውጭ ሀገር የሚደረጉ ፖለቲካዊ ጉባኤዎች ጠቀም ያለ የማዕከላዊው መንግሥት የፖለቲካ አቋም

ደጋፊ ሀሳቦች በማይገኙበት ሜዳ የሚካሄዱ ስለሆነ የተሟሉ ሊሆኑ አይችሉም። የሀገር ውስጡ የፖለቲክ ጉባኤዎችም ተቃዋሚዎችን የሚወክሉ ሀሳቦችን ስለማይጨምሩ ቁንጹል ናቸው። ተቃራኒ የሌለው ሀሳብ በቀላሉ የሚያረጅ የሚሰለችና ሟችነት ጠባይ ስላለው እንዴ ያለሌለው በቂ ሀልውና ይኖረኛል ብሎ በያስብ ለሀገር ሰላም፣ ለሕዝብ ህሊና እረፍት፣ ለዕድገትና ልማት አብይ መሰሏል መሆን ይችላል። በየትኛውም ዓይነት ድርጅት ቢሆን ተፃራሪና ተቃዋሚ ሀሳቦች እንዲሁም ግለሰቦች እንዴት መታየት፣ እንዴት መስተናገድ እንዳለባቸውና የማቻቻሉና የመቻቻል ዘዴ መዘየድ እስከልተቻለ ሁሌ በአንድ እጅ የሚጨብጨብ ስንኩልነት ድርጅቶችን እንደሚጋረጣቸው ተደጋግሞ ታይቷል።

ለሀገርና ለሕዝብ ዕድገት አስተዋጽዖ በሚያደርጉ የተለያዩ የሙያ ዘርፎች እኪያ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ በኢትዮጵያውያን በራሳቸው የሚካሄዱ ጉባኤዎች አሉ። በተለይ ሀገሪቱ ከሚያስፈልጋት የዕድገት እርምጃ አንፃር ሲታይ ብዙ ዓይነት ጥረት በተለይም አያሌ ተጨባጭ ጥረቶች እንደሚያስፈልጉ አጠያያቂ አለመሆኑ ስለሚታወቅ የሙያ ማህበሮች ሁሉ በየፊናቸው የየድርሻቸውን አስተዋጽዖ ማድረጋቸው የሚጠበቅ ነው። የሙያ ማህበሮች ጉባኤዎች እያዘጋጁ አበይት የሀገሪቱ ጥያቄዎች ላይ ውይይት በማድረግ የጉባኤዎቹን ውጤት እያሰተሙ ቢያወጡ ለጥናቶችና ለእድገት ሂደት መልካም እርምጃ ነው።

ለመደምደም ያህል የተለያዩ ዓይነት ጉባኤዎች የሚሰጡት ጥቅም ለእኩይ ተግባር ሊውል እንደሚችልም ከሞላ ጎደል ላይ የጠቀስን ሲሆን፣የተጠቀሱትንና ያልተጠቀሱትን ጥቅሞች በመመልከት በሀገር ውስጥና ውጭ ያሉ ያገሪቱ ዜጋዎች በማንኛውም ደረጃ ጉባኤዎችን ለህሊናችን ስፋትና ነገሮችን በጥልቅ ለመመልከቻ፣ እንዲሁም ለሀገር ግምባታ ተግበር ለማዋል በያሉበት ትህትናና ቅንነት የተመላበት እርምጃ እንዲወሰዱ ያለንን ሀሳብ እንሠነዝራለን። ስለ ሀገራችን ታሪክም ሆነ ስለተጋረጣት የተለያየ ችግር የውጭ ምሁራን የሚያካሂዱትን የጥናት ጉባኤ የምናደንቅ

**ቢሆንም፣ ዜጎቹ ማከሄድ የሚገባንን ተግባር ሌሎች እንዲያደርጉት መጠበቅ ድክመት መሆኑን ተገንዝበን ግዳጁን ለመቀበል የመንፈስ ዝግጅትና ብርታትን እንዲሁም ብቃትን ማሰደግ ተገቢ እርምጃ ነው እንላለን።**

---

**ይቅርታ**

**በአንዳንድ እክሎች ምክንያት ይህ እትም ዘግይቶ በመውጣቱ የመጽሔቱ አዘጋጅ ድርጅት ደንበኞቹንና አንባቢያንን ይቅርታ ይጠይቃል።**

**ምሥጋና**

**ቅጽ ፩ ቁጥር ፫ በማሠራጨት በኩል የረዱንን ተቋሞችና ግለሰቦች ከልብ እናመሰግናለን።**

<u>ማስታወሻ ፤</u>

<u>፩</u> የአቶ ብርሃኑ ድንቄን መጽሐፍት በቁጥር ፫ ላይ በምናስተዋውቅበት ጊዜ <u>እረሩ</u> የሚለውን የመጽሐፍ ርዕስ አስመልክቶ በተሰጠው ሐተታ ላይ << <u>እረሩ</u> ጸያፍ ቃል መሆኑን በመረዳት ደራሲው ... >> (ገጽ 79) የሚል ይገኝበታል ። አቶ ብርሃኑ እረሩ የሚለው ቃል ፀያፍ አይደለም ሲሉ ተቃውመዋል ። እረሩ የሚለው ቃል የሚያመለክተው << ኃይልን ፣ ንቃትን ነው ። በግራኛ (dynamic) የሚባለውን እኛ እረሩ እንለዋለን ። >> ሲሉ ደራሲው እንዲታረም ጠይቀዋል ።

<u>፪</u> <u>ሞረሽ</u> ቁጥር ፪ን በምናስተዋውቅበት ጊዜ የተደረገውን ግድፈት በመጠቀም ከዚህ ቀጥሎ ያለው እርማት እንዲደረግላቸው አዘጋጆቹ ጠይቀውናል ።
<u>የሰ.ወ</u> አገላለጽ ፡- << ደርግ ከጊዜያዊነት ወደቋሚ መንግሥትነት ፤ ከወታደራዊነት ወደ ሕዝባዊነት በመቀየር ላይ ስለሆነ ... >> ( ቁጥር ፫ ገጽ ፡ 84 )

<u>የሞረሽ</u> አዘጋጆች እርማት ፤
<< ደርግ ከጊዜያዊነት ወደቋሚ መንግስትነት ፣ ከወታደራዊነት ወደ ህዝባዊነት <u>እራሱን በራሱ</u> ለመቀየር የተለያዩ ሙከራዎችን እስካሁን ባለው የስልጣን ታሪኩ አሳይቷል ። >>
በተጨማሪም የ<u>ሞረሽ</u>ን ጽሑፎች ማግኘት የሚፈልጉ በዚህ አድራሻ መጠቀም እንደሚችሉ አዘጋጆቹ በደብዳቤአቸው ላይ ገልጸዋል ፤

MORESH

P.O.Box 564
Khartoum, Sudan

# ደብዳቤዎች

## ለሰምና ወርቅ አዘጋጆች

### የኢትዮጵያ ሳይንቲፊክ ሶሳይቲ መመሥረት

(Ethiopian Scientific Society, Inc..)

ሰምና ወርቅ ቅጽ 1 ቁጥር 3 ገጽ 63 ላይ ሠይፉ በላይ የፃፉትን «የኢትዮጵያውያን ሳይንቲስቶች የሙያ ማህበር አስፈላጊነት» የተሰኘውን ግሩም ዓምድ ተመልክቻለሁ። በአምዱ ውስጥ በጣም ወቅታዊ የሆኑ ነጥቦች አስፍረው ለአንባቢያን በማቅረባቸው ሊመሰገኑ ይገባል። በዚህ አጋጣሚ በአሜሪካን የምንገኝ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ሙያተኞችን ለማገናኘትና ለማደራጀት «ኢትዮጵያን ሳይንቲፊክ ሶሳይቲ ኢንኮርፖሬትድ» የተባለ ድርጅት እ.ኤ.አ. ዲሰንበር 1987 ዓ/ም ጀምር ያቋቋምን መሆናችንን መግለጽ እወዳለሁ።

ድርጅቱ በሜሪላንድ ስቴት የታወቀ፣ የግል ድርጅት ኮርፖሬሽን ነው።

### የድርጅቱ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፣

፩ኛ በዩናይትድ ስቴትስ የሚገኙ በሳይንስና በቴክኖሎጂ (ሕክምናን ያጠቃልላል) የተሠማሩ ሙያተኞችን ማስተዋወቅ፣ ማገናኘትና ድርጅት እንዲመሠርቱ የተቻለውን ሙከራ ማድረግ፤

፪ኛ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርት ተሠማርተው የሚገኙትን ተማሪዎች ትምህርታቸውን ጨርሰው በሥራ ላይ ከተሠማሩ ሙያተኞች ጋር እንዲገናኙና የሥራው ዓለም ለሚጠብቅባቸው ግዳጅ እንዲዘጋጁ ማድረግ፤

፫ኛ በአሜሪካ ያለው የሳይንቲፊክ ኮሚውኒቲ ጠንካራ የሆነ ድርጅት ከመሠረተ በኋላ ኢትዮጵያ ካሉት የሳይንስ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለአገሪቱ አስተዋጽኦ ለማድረግ መሞከር።

የመጀመሪያውን ዓላማውን ለሟሟላት የሳይንስ ዜና ጋዜጣ (newsletter) እና የሳይንስ ሙያተኞችን ስም ማውጫ (directory) ማተም እንዲሁም ሳይንትፊክ

ከሚኒቲውን በሚመለከቱ ጉዳዮችና በሳይንስ ጥያቄዎች ላይ ሴሚናሮች ማዘጋጀት ወዘተ ጠቃሚ መሣሪያዎች ናቸው ብሎ ድርጅታችን ያምናል። የስም ግውጫውን በሚመለከት ሶሳይቲው ከተቋቋመ ጀምሮ ብዙ ጥረት ያደረገ መሆኑን መግለጽ እወዳለሁ። ሆኖም ፎርሙ ተልኮላቸው ያልመለሱ አሉ። ጨርሶም ስለጉዳዩ ያልሰሙ እንዳሉ ግልጽ ነው።

ተማሪዎችን በሚመለከት፣ከሙያተኞች ጋር ከማገናኘት ሌላ በጣም ጥሩ ውጤት ለሚያመጡት ሽልማት በመስጠት፣ ፎተግራፋቸውና ውጤታቸው በአሜሪካ ለሚገኙ ኢትዮጵያዊያን እንዲደርስ መበተንና ማስታወቅ ለእውቀታቸው ምጥቀት፣ ለዝግጅታቸው ጥራት ይሰጠዋል ብለን እናምናለን። ለተሸላሚያቹ ከከብ ተማሪዎች ደግሞ ጥሩ ማበረታቻ ነው።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን አላማዎች ለመፈፀም ድርጅቱን ያቋቋምነው ብቻ ብቻችንን አንችልም። በአሜሪካ የምንገኝ የሳይንስ ሙያተኞች የወደፊት ዕጣ ምን ይሆናል ብለው የሚያስቡ በሙሉ እንዲተባበሩን ያስፈልጋል። በተጨማሪም ድርጅታችን የሳይንስ ሙያተኞች ድርጂት እንደመሆኑ መጠን ዓላማዎቹን ለመፈፀም ከፖለቲካ ነፃ የሆነና የፖለቲካ አቋም የማይወስድ መሆን ይኖርበታል።

በመጨረሻ (ስለኢትዮጵያ ሳይንቲፊክ ሶሳይቲ-ኢንኮርፖሬትድ) ለማወቅ የምትሹ፣ በተለይ ደግሞ ስማችሁ የሳይንስ ሙያተኞች ስም ግውጫ ላይ እንዲሰፍር ፎርሙ እንዲላክላችሁ የምትፈልጉ፣ እንዲሁም ሃሳባችሁን ልታካፍሉን የምትሹ በሚቀጥለው አድራሻ ፃፉልን።

Ethiopian Scientific Society
P.O. BOX 756
College Park MD 20740
U.S.A

ብሩክ ላቀው (የቦርድ አባል)

ይድረስ ለስምና ወርቅ መጽሔት አዘጋጅ፤

ለመላው ዓለም የቀረበው የፈደላት ገጽ በርከት የሚለው ከአቶ ተክለማሪያም ኃይሌ የተፃፈውን አንብቤ በጣም ተደንቂአለሁ። በመሰረቱ ከባዱን ነገር ማቃለልና ማሳጠር፣ ለዘመናዊ የኮምፒዮተርና የዕድገት መሣሪያዎችንም አመቺ ማድረግ በጣም የሚደገፍ ሐሳብ ነው። አቶ ተክለማሪያም ኃይሌም ለደከሙት ድካም መመስገን ይገባቸዋል። ይሁንና፤

1) የሃገራችን ፊደሰት ከሉበት ተቀንሰው በማንኛቸውም ቋንቋ ለሚገኙ ድምጾች በቂ ይሆናሉ ማለት ከንቱ ነው። ለምሳሌ በዓለም ጋዜጦች የኢራን ሃገር መሪ «አያቶስ ኾመኒ» ተብሎ ሲፃፍ የእንግሊዝኛው K ሆነ H አድርገው Homenie ወይም Komenie ብለው ሲጽፉት ድምጹ ስህተት ነው፤ ትክክለኛው ድምጽ ግን ከሳንቃ የሚወጣው ኾ የሚለው ድምጽ ነው። (ለማረጋገጥ የኢራንን ሰዎችን መጠየቅ ነው።)

2) በአጭር ጊዜ ለመፃፍና ለማንበብ የኮምፒዮተርንም መሣሪያ ለመጠቀም ያመቻል ለተባለው ምክንያት ሌሎችን የሰለጠኑ ሃገሮች (ለምሳሌ ጃፖንና ቻይናን) ብንመለከት በሺሕ የሚቆጠሩ ፊደሎች እያሏቸው ኮምፒዮተርንም ሆነ የማሕተም መሣሪያ ከመጠቀም አልተቸገሩም፣ ለሥልጣኔያቸውም እክል አልሆነባቸውም። በህንድ አገር በምቤይ በሚባል ከተማ ጥዋት ጥዋት ከአርባ በላይ በሆኑ ልዩ ልዩ ቋንቋዎችና በተለያዩ ፊደሰት የዕለቱ ጋዜጣ ታትሞ ይወጣል። ይሁንና በቅኝ የተገዙት ህንዶች እንኳን ፊደሎቻቸውን ለመቁረጥና ለመቀነስ የሚባል ሐሳብ የላቸውም።

3) አቶ ተክለማሪያም ኃይሌ ስለ ድርብ ፊደሰት ሆሄ ሲጽፉ «እስከአሁን ሲባዙኑና ሲንዘዙ የቆዩ ሞክሼና ዲቃሳ ፊደሎች» የሚል አነጋገር አስፍረዋል። ለመሆኑ ፊደሎች ይባዝናሉን? ፊደሎች ይንዘዘሉን? ተብሎ ቢጠየቅ መልሱ የለም ፊደሎች ከቶአይባዝኑም ነው በተቀደሚ ግን የፊደሰት ሆሄ ለምን አስፈለገ ተብሎ ቢጠየቅ ይህንን የሚያስረዳ መልስ እንሰጣለን።

በቅርቡ በአንድ ጽሑፍ ላይ «የደቡብ አፍሪካ ጥቁሮች አርነታቸውን መቸ ያገኙ ይሆን?» የሚል ጽሑፍ ማንበቤ ትዝ ይለኛል። ስሕተቱ አርነታቸው በሚለው ቃል ነው፣ ቃሉ ሐርነታቸው ሃርነታቸው ወይም አርነታቸው ተብሎ ለመጻፍ ሲቻል ምስቱም ግን ትርጉማቸው የተለያየ ነው።

ሀ)ሐርነታቸው፤ ሐርነት፤ ሐራ፤ ነፃ፤ ነፃነታቸው ማለት ነው።

ለ)ሃርነታቸው፤ ሃርነት፤ሃር፤የጨርቅ ዓይነት ነው

ሐ)አርነታቸው፤ፀያፍ ቃል፤አር፤እዳሪ፤ሠገራ ማለት ነው

እንግዲያውስ ፊደሰት ከየትና እንዴት መጡ፤ ለምንስ ሞክሼ ፊደሰት ሲፈጠሩ ቻሉ ብሎ ሳይመራመሩ ለመቆራረጥና ለማቃለል መቸኮል ተገቢ መስሎ አይታየንም። እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎችን እየጠየቅን ብንመራመር ግን የፊደሰችን መሠረታዊ ታሪክና ምንጭ ለማግኘት ይቻሳል።

በመደምደምያም የፊደሰት ሆሄን ለመቀነስ በመጀመሪያው መጽሐፋቸው

የተጠቀሙበት ደራሲ እንኳን በተቀደሚዎዋቹ አትሞች ስማቸውን ሲጽፉ ሐዲስ ዓለማየሁ ብለው ሐመሩን «ሐ» እና ዓይኑ «ዓ«ን ተጠቅመዋል። አሁንም ይኸው አቶ ተክለማሪያም ለዓለም የቀረበ ገጸ በረከት ሲሉ ዓይኑ «ዓ»ን ተጠቅመው፤ ስማቸውንም ሲጽፉ ሀይሌ እንደ ማለት «ኃ» የሚለውን ፊደል ተጠቅመዋል። ለውጥ ከራስ መጀመር አይገባምን?

ፊደላችን የታሪካችን አሳሪና ሰብሳቢ ገመድ እንደ መሆኑ መጠን እንዲሁ በቀላሉ የምንቆራርጠውና የምንቀንሰው እንዳይሆን መጠንቀቅ አለብን። ደግሞስ ኢትዮጵያ የፊደሏት ገጸ በረከት አቀረበች ስለዚህ ፊደላችንን ትተን እንቀበለው የሚል ሃገር እንግሊዝ ነው ወይንስ ሩስያ፣ ጃፖን ነው ወይንስ ቻይና፣ አሜሪካ ነው ወይንስ የዓረብ አገሮች? ይልቅ ያለንን ስንቆራርጥ ባዶአችን እንዳንቀር መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ደግሞስ ኢትዮጵያ እጅና እግሩዋን የቆረጠች ጥንታዊ ቅርስ የሆነውን ታሪካዊ ፊደልዋን እየቆረጠች እንድትለግስ ለዓለም ገጸ በረከት ይቅረብ የተባለው ከወዴት ዩኒቨርሲቲ ይሆን?

የጽሕፈት መኪና (ታይፕ ራይተርም) ቢሆን ኮምፒዩተርም ቢሆን ያለ ምንም ችግር በሙሉ የኢትዮጵያ ፊደላት እየሠሩ ነውና ከመቁረጥና ከመቀነስ አስቀድሞ መመራመርና ታሪክን ማጥናት የፊደላትን አመጣጥ ማጥናት ያስፈልጋል።

ኢያሱ ጎርፉ
ሎስ አንጀልስ

ከላይ ለተጠቀሱት ነቃፊ የተሰጠ ማብራሪያ
ከተክለማርያም ኃይሌ

የሰውን ልጅ ሰው የሚያሰኘው አንድ ሰብአዊነቱ ቢሆንም በጥቁረት፣ በቅላት፣ በብሔነት ወይም በእምነትና ባህል ረገድ የተለያየ ጠባይ እንዳለው እንገነዘባለን። በዚሁም አንፃር የ « ሀ» ፊደልነት የሚወከለው በአንድ የ «ሀ» ሌጣ ድምጽ ብቻ አይደለም። አረቦችና አካባቢያቸው በማጎርናት ማለት በላንቃና ጉረር ወይም በተለያዩ የትንፋሽ ስሌቶች ይጠቀሙበታል። ኢትዮጵያዊውም በኢትዮጵያዊነት ባህርዩ (ያውም በተለያዩ ነገደ ብሄሮች ድምጽ) አውርፓውያንም በዚያው አህጉር ጠባይ በማጣቀስ ማለት "ሀ" ለአንድ አገር ወይም ክፍለብሄር እንደጉልማ ተነጥሎ የተሰጠ መጠሪያ ድምጽ ስለማያገኝ የተነጠረና የተበጠረ ውሳኔ አልተሰጠውምና ሁሉም በየፈናው እንደመጣጡ ይገለገልበታል። ነቃፊው የድምጾችን መለያ ውስጠ አዋቂ ከሆኑ የኛዎቹ ለስት "ሀ" ዎች ሁለት "ሰ"ዎች "አ"ዎች ሁለት "

ፀ"ዎች እንዴት እንደተለያዩና እንዴትስ እንደሚጠሩ ማስረጃውን ያቅርቡልን።

የአማርኛችንን መዝገበ ቃላት ደራሲና የአለቃ ኪዳነወልድ ተክሌን የግእዝ መዝገበ ቃል ያወጡትን አቶ ደስታ ተክለወልድን በ1967 ማለት ከአስራ ስስት አመታት በፊት ስለድርብ ፊደሎች አፃፃፍና የድምጽ አለያየት የሚነገር ደንብ እንዳለና እንደሌለ እነጋገራአቸው ምንም እንደሌለ አስረድተውኛል (እሳቸው ግን ከኖሩው ልማድ እንዳማያፈገፍጉ ነግረውኛል) ስለዚህ ሀሌታው "ሀ" ሐመሩ "ሐ" ብዙኃኑ "ኀ" ንጉሡ "ሠ" እሳቱ "ሰ" አልፋው "አ" ዐይኑ "ዐ" ፀሐዩ "ፀ" ጻድቁ "ጸ" በጥንት ዘመናት የተለያየ ድምጽ ነበራቸው ቢባልም አሁን ደብዛው ጠፍቶአል።

ነቃሬው ትዝ እንዲሉቸው የምፈልገው ነገር ቢኖር ስልጣኔን በተቀዳሚነት ያፈለቁት ምስራቃውያን በሁዋላ መጡ በአውሮፖውያን የተበለጡትና ወደሁዋላ የተጎተቱት አንደኛው እንጋሩ ምክንያት እንደሳቲኑ ያለ ቀላል ፊደል በማገናዘብ ፈንታ በጥንቱ ውስብስብ ፊደሎችና ስእለቃላት ወይም ስእለአሳብ (ideography) ሲንገታገቱ በመቆየት በችኮመንቻካነት ሳቢያ ህዝባቸውን በቀላሉ ለማስተማር ባለመብቃታቸው መሆኑን በጽሞና ማጤን ይጠቅማል። ለምሳሌ ጽንታዊውም የቻይና ቤተ መንግስት ነክ ዘሮችና ደብተራዎች ተራው ሰፊ ህዝብ ከነሱ ጋር በእውቀት እቻ ሆኖ የሹመት ወንበር እንዳይሳተፋቸው ስእለቃላትን የሙጥኝ ብለው በስውርና በድብቅ ይዘው ሲሸሞነሞኑ መኖራቸውን ከታሪካቸው እንረዳለን። በነሱ አካባቢ ያሉት አገሮችም ተመሳስይ ጽዋን እየቀመሱ በዚያው ጦስ ተንገላተዋል። ባሁኑ ጊዜም ቢሆን ሲያወላዳቸው የሚችለውን የላቲን ፊደል ለመገናዘብ ፈራ ተባ እያሉ ናቸው። እስከዚህም የተመረሩበት ምክንያት አሁንም ቢሆን ስነጽሁፋቸውን አበክሮ ለማወቅ ዘመነዘመናትን የሚፈጅ መሆኑን እዚያው ፔኪንግ-ቻይና ስድስት አመት በተቀመጥኩበት ጊዜ ውስጥ አስረድተውኛል። በምስራቃዊነት ሙጥኝባይነትና አሞተቆራጥነት እስከሁን የተደረሰበት ሀይለጽሀፈትም (Computer) ቢሆን ቀላል ፊደልን እየናፈቀና እየቿመጠ ነው። ስለዚህ እኔ ያወጣሁት ከአራት ሰረዞች ብቻ (| - / \) የተገጣጠመው ፊደል ፈውስዱውያን ነውና አባዚዎችን ሁሉ አበር ተምች ይመታቸዋል ቢባል ከሀቅ የራቀ አይደለም።

አፄ ምኒልክ አዲስ ፊደል ለመፍጠር የተፍጨረጨሩት እንዲያው ለይስሙላ አልነበረም፤ የአለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ ሙከራም ትናንትና ነበር። በዚህ ሀይለ ግንባር ላይ መለለፍም እንድቀን ድልን ይዞ ብቅ ማለቱ አይቀርም። የሚያመናታ ጉዳይ አይደለምና የሚጠብቀው "በ ጊዜ ለኩሉ" ብቻ ነው። እንግዲህ ነቃሬውን በድጋሜ የማሳስባቸው ቀላል ፊደልን በጊዜው የቀሰሙት አውሮፖውያን በቀላሉ

ቶሎ ቶሎ እውቀትን እየሰቀሙ በቀሏሉ ለወገኖቻቸው በማስተላለፋቸው ሌሳውን አለም አሽቀንጥረው ጥለው እነሱ በስልጣኔ ግስገሰ እንደፈረጠጡ ለማየት ምርግሬ እንዲያደርጉ ነው።

አብዛኛው አለም የወረሳቸው የህንድ አህዞች 1-2-3-4-5-6-7-8-9-0 ለመላው አለም ህዝብ የቶጠራ ፈውስ መሆናቸው የሚያጠያይቅ አይደለም። ስለዚህ ቀላል የወል ፊደል ከተፈጠረ መላው አለም ተቀብሎ ቢጠቀምበት መግባበትንና አንድነትን ከማበርከቱም ሌላ ትምህርትንና የእውቀትን ደረጃ ለማፋጠን በቀላሉ ይረዳል።

ሌሳውን ለጊዜው እንተወውና በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንኳን "How are you" ንና "ሃው አር ዩ"ን ብናስተያያቸው የነሱ አፃፃፍ የማያስፈልጉትን ፊደሎች "O-E"ን ጨምር ስምንት ፊደሎችን ሲውጥ የኛው ግን በአምስት ብቻ ይገሳገሳቸዋል። ለዚያውም ቢሆን የነሱ "O" ወደኛው "ኣ" ተለውጦ መነበብ ስላለበት ውጥንቅጡ ወጥቶአል። ለምሳሌ Seep-Seat-Sinck-Seize በአንድ "ሲ" ሀይለድምጽ መገልገል ሲችል በሰበት የ"ኢ" ድምጾች ገራ ተጋብቶታል። ይህም የዘልማድ አፃፃፍ እንጂ ቀዋሚ ደንብ የለውም።

በሌላ አነጋገር ደግሞ የግብጽ ቤተክርስቲያን ኢትዮጵያዊ ሊቀጳጳስ መሾም አይገባውም ብላ አይንዋን አፍጣና ወገቡዋን ገትራ ከተከራከረች በሁዋላ ተረታች። ሌላው አለም አሜን ብሎ ከተቀበለው የኛውስ ፊደል ለጠቀሜታ ቢውል ምን ያከራክራል? የሮማ ቤተክርስቲያን በእርጅናው ዘመናት ጋሊሊዎን ምድር ጠፍጣፋ ናት ብለህ እመን ያለበለዚያ ወህኒ ቤት ትበሰብሳለህ ብላ ስለቸከቸበት አዎን ጠፍጣፋ ናት ትሁንላችሁ (በለሆሳስ) ደግሞ ትሽከረከራለች) ብሎ ከአደባባዩ ተሰናበታቸው። እንዲሁም E=MC2 አውደቀመር (Formula) እንደወጣ ብዙ የሀይለጥበብ (Physics) አዛውንቶች ተጠራጠሩ አሁን ግን በዚህ አውደቀመር በመገልገል አለም ጠፈርን ያስስበታል። ሀይለኢፍላየንም (Atomic energy) እየመቷበት ነው።

አምስቱ ሀይለድምጾች (Vowels)=a, e, i, o, u ግማሽ ሚሊዮን ያህል የእንግሊዘኛ ቃላት ምንም የድምጽ ደንብና የአጠራር ስርአት ሳያወጣላቸው ከሚሊዮን በላይ የሚበልጡ ድምጾችን እንዲወክሉ ስለተገደደ Spelling የሚባለውን ጣጣ ዘመነዘመናትን እየፈጀ ነው ሲያቅተንም ወደ መዝገበቃላት እንሮጥአለን። ALTHOUGH, TOUGH, DOUGH, DINE, DIN, PSYCHOLOGY ለምን ያለመልከቻውና ያለደንባቸው ተምታትተው እንደዚህ እንደተጻፉ ማስረጃ የለም። ስለዚህ አዲሱ ፊደል ነቃፊውን ያሳስበውን የእነ Khomeni እና ሌሳውንም ጦስ ሁሉ

እግበስብስ ከጣጣና ፈንጣጣ እንደሚያወጣን አልጠራጠርም።

በተለየም በስስተኛው ክፍለአለም ከተመደብነው አብዛኛዎቻችን ጥቁር አፍሪካውያን ጥበብን የምንመዘግብበት ቀለልም ሆነ ነበር ፊደል ስለሌለን ባለህበት እርገጥ ሆኖአል። ቀደም ቢልማ ቅኝገዢዎች እንደልባቸው ፈንጭተውብናል። ቅርስም ቢሆን ባዲስ ፊደል አማካይነት እየተቀዳ ይቀመጣል እንጂ ነቃፊው እንደሚሉት ሊቆረቆዝ አይችልም። ታዲያ ተጎልቶና ተወዝፎ ከተፈራማ ሰይጣኔ ይሆንና ፍንክች ያበ ቢላዎ ልጅ ይሆናል። አሁን በስልጣኔ ሰይ የሚፎልሉት አበይት አገሮች ያንን ዱሮ የተጫጫረና የተሞነጫጨረ ውጥንቅጡ የወጣ ፊደላቸውን በጊዜው መስመር አስይዘው እልባት ስላደረጉለት ምን ተጎዱ? ሌላውንስ ወገን በማቁዋሸሽ የሚያዩትና የሚጸየፉት ስነጽሁፋቸው ስለዘባነናቸው አይደለም ወይ?

የሰው ልጅ ሁሉ የተሰማራበት ማንኛውም ነገር በየጊዜው መሻሻልና መሰንገል አለበት። «በጋሻና ጦር እንጂ ባዲሱ መሰሪያ አልዋጋም።»፣ «በዱሮ አሮጌ ተሸከርካሪ እንጅ ባዲሱ ቀልጣፋ ነገር አልቀመጥም»፣ «በዱሮ ትኩል ቤት እንጂ አዲሱ ውስጥ አልኖርም»፣ «በየጥሻው ውስጥ እንጅ ቀንጥር በሌለበት አውራ ጎዳና አልጉዋዝም»፣ «በድሮ ፊደል እንጅ ባዲሱ አልጽፍም»፣ «በባለእርግብግቢቱ (Propeller) እንጅ በጀት አውሮፕላን አልበርም»፣ «የጥንቱን ባህልና ልማድ እንጅ አዲሱን አልቀበልም እምቢ ! አሻፈረኝ! አኪኪዘራፍ ምንቸገረኝ ድፊው ደንቅሪው አሽቀንጥረው» ከሆነማ አሁን የምንፈሰስሰባቸው ምቾቶቹ ሁሉ ባልተገኙም ነበር።

ነቃፊው ባልጠበቁት ፊደል ስሜን ተጽፎ ስለማግኘታቸው ጉዳይ የመጽሄቱ አዘጋጅ ሊያስረዱዋቸው ይችላሉ በኔበኩል ግን አሁን ለጊዜው አዋጅ አልወጣምና በየትኛውም«ሀ»-«ሐ»-«ሃ» ቢፃፍ ምንም ፋይዳ የለውም።

ከአዘጋጆቹ

አቶ ተክለማርያም ያባታቸውን ስም ያስፈሩት "ሀ"በመጠቀም ነበር ነገር ግን በመኪና በምንመታበት ጊዜ በ"ኃ"ፊደል (ቁጥር ፫ ገጽ 32) መቅረቡ የኛ ድርጊት መሆኑን እንገልጻለን፤በማውጫው ላይ ደግሞ "ሀ"ጥቅም ላይ መዋሉን እናሳስባለን።

ለሰምና ወርቅ አዘጋጆች

ለማንበብ ፍላጎት እያለን የአማርኛ መጽሐፍት ለማግኘት የተቸገርን ሰዎች መኖራችን እያጠራጥርም ስመ ጥሩ ደራሲዎቻችንም የፃፏዋቸውን በርከት ያሉ መጽሐፍትን ያንባቢ ያለህ እያሉ መርከቶ ፀሐይ ሲመታቸው ይውላል ጨርሶ ለመታተምም ዕድል ያላገኙና ብቅ ብለው የጠፉም አሉ

መጽሐፍቶቻቸውን መጽሐፍት ለማድረግ ደራሲዎቻችን ብዙ ችግር ከሰለፉ

በኋላ አንባቢ (ገዢ) በማጣት ብቻ ሙያቸውን ረግመውና በማይፈልጉት የሥራ መስክ ተሰማርተው እንዲኖሩ መገደዳቸው ዕሙን ነው።

ታድያ እናንተ (የሰምና ወርቅ አዘጋጆዎች) የሚቻሉችሁ ከሆነ ለሙከራ ጥቂት መጽሐፍት እስመጥታችሁ (አስፈላጊ ከሆነ አራብታችሁ) አንባቢንና መጽሐፍትን ብታገናኙ ምን ይመስላችኋል? ይህ ተግባር ለደራሲዎቻችን የገንዘብና የሞራል ድጋፍ ከመስጠት ሌላ በሙያቸው ሠርተው የበለጠ ፍሬያማ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል።

አገራችን ቡና እንጂ ፀሐፊ የማታበቅል ይመስል በውጭ አገር ፀሐፊዎች ለተለከፉትም አንባቢዎች አማራጭ ማቅረቡና ማሳየቱ መልካም ይመስለኛል።

ሙሃመድ አሊ

ሳስካቹን ፤ ካናዳ

ከአዘጋጆዎቹ፤

ሀሳብዎን በአድናቆት ተቀብለናል። በየመጽሔቱ ድርጅት እስኪጠናከር ድረስ በመጽሔቱ ቁጥር ፫ ላይ እንደሳሰብነው ደራሲያን ጽሑፎቻቸውን በምዕራፍ በምዕራፍ በማውጣት ትችት እንዲደረግበት ቢያደርጉ መጽሐፋቸው ውሀደት ያለውና የተቀነባበረ እንደሚሆን ያለንን ሀሳብ ዘርግተናል። በሌላ በኩል ደግሞ የተፃፉ መጽሐፍት በመጽሔቱ ሰቢያ መተዋወቅ እንደሚችሉ ገልጸናል። ደራሲያን ማውጣት የሚፈልጓቸውን ጽሑፎች አሁንም ከአዘጋጀው ክፍል ጋር በመመካከር ሀሳብ ለሀሳብ መለዋወጥ ይችላሉ። መጽሐፍትን ከደራሲዎች በመረከብ የማሰራጨቱን ተግባር አሁን ባለንበት ደረጃ ብዙት ባለው ሁኔታ የማንችል ቢሆንም በመጠኑ በማከናወን ላይ ነን። በቅርብ ጊዜ የደረሱንን <u>*በረከተ መርገም* እና *የበሰለው ይራል*</u> የተሰኙ መጻሕፍት በማሠራጨት ላይ እንገኛለን።

ለሰምና ወርቅ አዘጋጆዎች

አዲስ የመጽሔታችሁ (ተከታታይ) ደንበኛ ለመሆን የምፈልግ ኢትዮጵያዊ ከኒውጀርሲ።

ለመጽሔታችሁ የምጽፋቸውን ጽሁፎች ከስራቸው Mr. Pen የሚል ታዩ ይሆናል ይህ የኔ የጽሁፍ ስሜ ስለሆነ አትደነቁ። ይህን ስሜን አዲስ አበባ ሳለሁ ለብዙ የሬድዮ ፕሮግራም ስጽፍ ተጠቅሜበታለሁ።

ሰምና ወርቆች ከአለፈው እትማችሁ ሌላ መጽሐፋችሁን ሙሉ በሙሉ አንብቤአለሁ ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም። መጽሐፋችሁ በኔ በኩል ከአንድ

ጉልህ ችግር በቀር ሌላ ምንም ያለው አይመስለኝም። ይህ ችግር መስሎ የታየኝ ነገር መጽሀፉችሁ ይበልጡኑ ተወዳጅ እንዲሆን ከሳይንስና ከምርምር ጽሁፎች ጋር ቅኔዎች፣ ግጥሞች፣ ልብ ወለዶችና እውነተኛ የሀገራችንጀግኖች የህይወት ታሪክ ቢታከልበት መጽሀፉ አሁን ካለው የአንባቢ ፍላጎት በተጨማሪ የብዙ አንባቢያንን ፍላጎት እንደሚስብ አልጠራጠርም።

ይህ የአንድ አንባቢያችሁ ምክር እንደመሆኑ መጠን ሰታነቡትና ሰትወያዩበት አትቀረም ሆኖም ይህን ምክር ተቀብላችሁና ተስማምታችሁ ጽሁፎችን ልትጀምሩ ከተዘጋጃችሁ የመጀመሪያው ተሳታፊ ለመሆን ስለምፈልግ ይህንን የቅኔ ምልልስ ጽፌላችኋለሁ።

MR. Pen

ከአዘጋጅው ክፍል፣

በቁጥር ፩ ላይ ባዘጋጀነው መንደርደያ ላይ ስለሥነጽሑፍ ስንዘረዝር ግጥሞች፣ ልብወለዶችና የመሳሰሉት በሃገራችን መሬት ያቆጠቆጡ ልሳኖችና መዝናኛዎች ከፍ ያለ ቦታ እንደሚጣቸው ያለንን ሀሳብ ገልጸን ነበር። የብዙ አንባቢዎቻችንንም ሀሳብ ስናዳምጥ ግጥሞችና ልብወለድ ድርሰቶች በመጽሔቱ ሰቢያ እንዲቀርቡ በተደጋጋሚ ተገልጾልናል። በመሠረቱ ስምና ወርቅ የምርምር መጽሔት እንደመሆኑ መጠን ግጥም መግጠም ፤ ድርሰት መጻፍና ልብወለድ ታሪክ መድረስ የሚችለው እንዲሁም እንደርሰዎ ቅኔ መቀኘት የሚችል ደራሲ ለለግጥም አገጣጠም ስልት ፣ ስለልብወለድ ታሪክ አዘገጃጀት ስለቅኔ አደራደር ዘዴ እንዲጽፍ ይጠበቃሉ። እንዲሁም ግጥም ገጣሚ የራሱን ስልት ከሌላው ደራሲ ስልት አስተያይቶ ትችት በማቅረብ የምርምሩን አድማስ ማስፋፋት ይችላል። በልብወለድ ድርሰት ለይ ትችትና አቃቂር በመጻፍ ይዘቱን አጉልቶና አሳድጎ ማቅረብ እነዚህንና የመሳሰሉትን ይዘቶች እንጠብቃለን። ይህ በሚሆንበት ጊዜ የሥነጽሑፍ አጠቃላይ ይዘት ፣ ለዛ ፣ ቃናውና የጽንስ ሀሳብ ከምቸት ይበልጥ ዳብሮ አያሌ ደራሲያንን ለመሳብና ምርቱም ከፍ ማለት ይችላል። አዳዲስ የአቀራረብና የአጻጻፍ ስልቶችና ዘዴዎች ሊፈጠሩ የሚችሉት በዚህ መንገድ መጊዝ የተጀመረ እንደሆነ ነው። እስዚያ ጥቂት ደራሲያን ብቻ መድረኩን ይዘው ተደጋጋሚና አሰልቺ እየሆነ የሚሄደውን ጽሑፋቸውን በአንባቢው ላይ ይጥሉበታል። ዋናው አላማችን ምርምራዊ ጥናት ለማስኬድ ቢሆንም እስካሁን በየእትማችን ግጥምና ልብወለድ ሥነጽሑፎችን በማስተናገድ ላይ እንገኛለን። ወደፊት በልዩ እትም ድርድራችን ላይ የስነጽሑፍ እትም የማውጣትም ሀሳብ አለን። ቅኔዎን እትመናል።

ይድረስ ለሰምና ወርቅ አዘጋጆች፤

ከሁሉም በማስቀደም የከበረ ሰላምታዬን እያቀረብኩ ራሴን ለማስተዋወቅ ያህል ናይሮቢ ፣ ኬንያ የምኖር መሆኔን እገልጻለሁ። ውድ የመጽሔቱ አዘጋጆች ፤ ጥር 1979 ዓ. ም በተዘጋጀው ቁጥር የሚገኝ ጽሑፍ ጫት በኢትዮጵያና በአንዳንድ የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች እንደሚበቅል ይጠቅስና ጫት ለ501 በሽታዎች መደሐኒትነት እንደሚውል ያብራራል። ጥያቄዬ ጫት ለብዙ በሽታዎች ፈውስ መሆኑ በሊቃውንት ዘንድ ተረጋግጧል ወይ ነው። ከተረጋገጠ በጥቂቱም ቢሆን ለምን ለምን በሽታዎች እንደሚጠቅም ብታስረዱኝ።

ማህሙድ አመር ማሐመድ

ከኬንያ

ከአዘጋጆች ፤

በአገራችን በተለምዶ የተፈጠሩ መድሐኒቶች ብዙ ቢሆኑም ሚስጢራቸውን ጠልቶ የሚያውቅ በጣም ጥቂት ነው። ጥቅሱን እንዳለ የወሰድነው የአዲስ አበባ ዮኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናት ኢኒስቲትዩት ስምንተኛው የኢትዮጵያ ጥናት ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ ከቀረቡት የተሰበሰቡ ሥራዎች ላይ ነው።

(ኅዳር ፲፯ ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፯) በሐረር አካባቢ ጫት ለ501 በሽታ መድሐኒትነት እንዳለው ከመታወቁ ሌላ የቀረበ ማስረጃ በአረብኛ ጋት (Ga-at) ተብሎ የቀረበው የቁጥር ፎርሙለ (400+100+1) መሆኑ ነው። ወጣም ወረደም ከጉባዔው ዋና ዓላማ እንደተረዳነው ከሆነ፤አንደኛ / በተለምዶ የተፈጠሩ መድሐኒቶች ምስጢር የወላጆች ትውልድ ከማለቁ በፊት መፈልፈል፣ ሁለተኛ / እነዚህ የተለምዶ መድሀኒቶች ላይ ሳይንሳዊ ጥናቶች ማካሄድና ፍቱንነታቸውን ማረጋገጥ ወይም መሰረዝ፣ ነው ሰስተኛ / ደግሞ መድሐኒቶቹ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚሸሻሉበት ዘዴ ካለ ማሻሻል ፣ ለጤንነት አደገኛነት ካላቸውም አደገኝነቱን ማስተማር ነው። በአንድ ቃል ግን የተለምዶ መድሐኒት ዘመናዊ የሳይንስ ጥናት እስኪልተካሄደበት ድረስና ጥቅሙና ጉዳቱ በሚገባ እስከ ሊታወቀ ድረስ መወሰድ አይኖርበትም። ስለ ጫት ጠለቅ ያለ ዕውቀት እንዲኖርዎት ከፈለጉ የሚቀጥሉትን ጽሑፎች ፈልገው እንዲያነቡ ምክር እንሰጣለን።

1. Flueckiger, F.A. and J.E Gerock 1887. Contrribution To the Knowledge of Catha Leaves. Pharm . J . Transy. 18,221

2. Wolfes, 0. 1930 Veber das Vorkmmen Von d-

Norpsendoephedrin in Catha edulis. Arch pharm , 268,81.

3. Szendrei, K 1980 The Chemisty of khat. Unbull on Narcotics 23,5.

4. Kalix, P. 1984 The Pharmacology of Khat. G.G.N Pharmac., 15, 179

ጅቡቲ 10- 3- 88

ለሰምና ወርቅ አዘጋጅ

ቀሽንግተን

«የሰምና ወርቅ» መጽሔት የመጀመሪያው ቁጥር ዛሬ ካንድ ወዳጄ እጅ አገኘቸ በታላቅ ደስታ ከዳር እስከዳር ሳነበው ቻያለሁ። በጣም ጥሩ መጽሔት ነው። ስመሥራቾቹ አድናቆትንና የደስታ ስሜቴን አገልጻለሁ። ለወደፊትም ዓላማው እንዲሳካ መልካም ምኞቴ ነው።

ሆኖም አንድ ለመቀበል ያስቸገረኝ ነገር ቢኖር የመጽሔቱ ስም ነው። «ሰምና ወርቅ» የሚል ርዕስ የተሰጠበት ምክንያት «ቅኔ፣ እንዲሁም ሰምና ወርቅ የተባሉ ቃላትና ገለፃዎች ምን እንደሆኑ ትኩረት ሰጥተን እንድንመለከት ለማሳሰብ የተደረገ ነው» ይላል። በሌላ በኩል ደግሞ መጽሔቱ ለማንኛውም ሰው ስለማንኛቸውም ጠቃሚ ጉዳይ ምርምርና ጥናት እንዲሁም ለውይይት ነፃ መድረክ ይከፍታል ይላል። ይህም ማለት ማንም ሰው ስለማንኛቸውም ጉዳይ በግልጽ እነጋገር ሃሳቡን ለመግለጽ የሚችልበት መጽሔት ነው። በርግጥ አንዳንዱ ሰው ቅኔም ሆነ ሰምና ወርቅ ጽሑፍ ማስፈር ይችላል። ሆኖም ለመንደርደሪያ እንዲሆኑ ተብለው የተሰጡትን አርእስቶች ስንመለከት አብዛኛው ጽሑፍ በግልጽ አማርኛ እንደሚሆን ይጠበቃል። መጽሔቱን «ሰምና ወርቅ» ብሎ መሰየሙ ዓላማውን ከጠቅላላ ጉዳይ ወደ ስነጽሑፍ ማጥበብ ይመስለኛል። የሆነው ሆኖ ከስሙ ምን አለ?

ክሣሁን እሸቴ

ከአዘጋጀው ክፍል፤

ለመጽሔቱ የተሠጠውን ስያሜ የመጽሔቱን ይዘትና ዓለማ የሰምና ወርቅ ጽንሰ ሀሳብን ምንነትና ዝምድና ላይ የሚያተኩር ጥያቄ ስለሆነ በየነጥቡ ለማብራራት እንሞክራለን።

መነሻ ዓላማችን መጽሔቱ የምርምርና የጥናት መጽሔት እንዲሆን ነው። ምርምርና ጥናቱ በኢትዮጵያ ላይ ያተኮረ እንዲሆንም ዓላማ አድርገን ተነሥተናል። ይህን ዓላማ በሚገባ ለማስጨበጥ የመጽሔቱ ርዕስ ሀገር በቀል በሆነው ብዙ ትርጉም ባዘለ ለአያሌ ገለጻዎችና ማብራሪያዎች መጠቀሚያ ሊሆን በሚችለው እንዲሁም ወደፊት ጥልቅ ጥናት ሊደረግበት ይገባል ብለን በምናስበው በቅኔ ቤት አከባቢ ላይ እንዲመሠረት ባደረግነው ፍለጋ ሰምና ወርቅ የሚለው ስያሜ አጥጋቢ ሆኖ አገኘነው። እርስዎ ካነሷቸው ጥያቄዎች አንፃር ሲታይ አጥጋቢነቱን በጭሩ ለማስቀመጥ ግልጽና ምሥጢራዊ ገለጻዎች በቅኔ ሥነ ጽሑፍ እንዴት በሰምና ወርቅ አምሳል እየተቀረጹ እንደሚወጡ (እንደሚመረቱ) መመልከትና ለመረዳት መሞከር በቂ ፍንጭ ይሆነናል። በሰምና ወርቅ ቅንብር ውስጥ ግልጽና ድብቅ(ሚስሥጢራዊ) አገላለጽ ተዋሀዶ ባንድነት ይገኛል። ሰሙ ወርቁ እያልን የምንፈታው ሁለት አገላለጾችን አቅፎ ስለሚገኝ ነው። ላይ ላዩን ለሚያየው ቅኔ ስንል ሰምና ወርቅ እንዲሁም ውስጠ ወይራ ---- የሚሉ ቃላት እንዲሁ ተቀብለን የምንጠቀምባቸው ናቸው። ጠለቅ ብሎ ለሚመራመር ግን ለምን የሰም አገላለጽ ሰም የወርቅ አገላለጽ ወርቅ ተባለ ብሎ መጠየቅ ይገባዋል። ለምን የሰምና ወርቅ ምሳሌ ተፈለገ ሆነ ነገሮችን ሁኔታዎችን ታሪክን ፍልስፍናን ሥነ ፍጥረትን ወዘተ ለመግለጽ። ከተራ ገለጻና ከተራ ትርጉማቸው ግደ ጠለቅ ያለውን ገለጻና ትርጉም በምንመረምርበት ጊዜ እነዚህ በዝቅተኛ ደረጃ ጥቅማቸውና ፍቻቸው ተወስኖ የሚገኘው ጽንሰ ሀሳቦች ከፍተኛ ወደሆነ ጥቅምና እውቀታዊ አድማስ መሸጋገርያ ድልድዮች እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል።

ስለዚህ ሰምና ወርቅ የሚለው ስም በሥነ ጽሑፍ መስክ (በግጥምና በልብ ወለድ ድርሰቶች) ብቻ ተከልሎ መታየት የለበትም። ጥልቅ የሆነ ፍልስፍናዊ ይዘትም አለው። ሌሎችም ተመሳሳይ ጽንሰ ሀሳቦች በቅኔ ፍልስፍና ቤት ሞልተዋል። እያንዳንዱን ቃል ሆነ ጽንሰ ሀሳብ ከተራ ፍቺውና ከተራ ገለጻው በሻገር ጠለቅ አድርጎ በመመርመር ጠለቅ ያለ ገለጻውን ፍቺውንና ተግባሩን ለማግኘት ይቻላል፣ ይገባልም። ይህ ዓይነት አጠናንና አመራመር በዕውቀት መስክ ራሱን ከመቻል ጋር የተዛመደ ጥቅም እንዳለው ጭምር መታየት አለበት። ስለዚህ እርስዎ እንዳስተዋሉት ሰምና ወርቅ መጽሔት ግልጽና ሚሥጢራዊ ገለፃዎች ባሉት ጽንሰ ሀሳብ ላይ የተመሠረተ ነው። ፍጥረትንም ሰውንም እንዲሁም ማንኛውንም ክስተት በምናጠናበት ጊዜ የነዚህ ቅራኔዎች ውህደት ሰምርበት ይታያል።

# የብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል

## የሕይወት ታሪክ



«. . . ሥርና መሠረት ያለውን ያገርን ልምድና ጠባይ
በጭራሽ መተውና መልቀቅ ዝክረ ነገሩን መርሳት
ለሰው ልጅ የተገባ ተግባሩ ሆኖ አይታይም።. . .»

ዝክረ ነገር

ከአዘጋጁው ክፍል፤

በሀገራችን በኢትዮጵያ አበይት የዘመናችን ደራሲያን በመባል ከታወቁት መሃከል ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል አንዱ ናቸው። የመንግስት አስተዳደር ሃላፊነትን ከምሁራዊ ተግባር ጋር በማቀናጀት ለሰውና ለመጭው ትውልድ መገለገያ እንዲሆኑ የደረሷቸው መጽሐፍት በይዘታቸውና ባቀራረባቸው በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ ለእያሌ ዘመናት ዘልቀው የሚቆዩ ናቸው።

የመልእክቶቻቸው ሐገራዊ ይዘት እንዲሁም የሥራዎቻቸው ዕውቀታዊ አዝማሚያ ለእያሌ ትውልድ መልክም መነሻ በመሆን ያገለግላሉ።

ከዚህ ቀጥሎ የታተመው ራሳቸው ያረቀቁት የሕይወት ታሪካቸው የተገኘው ከቤተሰቦቻቸው ሲሆን፣ የሕይወት አመራራቸውን በቅርብ ሆነው የተከታተሉ ቤተሰቦቻቸው የፃፉት መግቢያ ጽሁፍ አብሮ ቀርቧል። ይህን ሠነድ አግኝተን በማተማችን ለቤተሰቦቻቸው አድናቆትና ምስጋናችንን እንገልፃለን።

የዚህ ሰነድ መታተም ከምርምር ሂደት አንፃር ብዙ ጥቅሞች አሉት። የብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴን የሕይወት ታሪክ ማወቅና ማግኘት ለሚሹ ተመራማሪዎች፤ ታሪክ መዝጋቢዎችና የሕይወት ታሪክ አቀናባሪዎች በጣም መነሻ ነው።

## የብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል አጭር የሕይወት ታሪክ

ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መሥቀል ከክቡር ፀሐፊ ትእዛዝ ወልደመስቀል ታሪኩና ከወይዘሮ ደስታ አየለ ጥቅምት 19 ቀን 1897 ዓም አዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ።

ከ1904 እስከ 1906 ዓም አባት እናታቸው ቤት መምህር ተቀጥሮላቸው መሠረተ ትምህርት ሲከታተሉ ቆይተው ከ1907 እስከ 1913 ዓም በዳግማዊ ምንሊክ ትምህርት ቤት የፈረንሳዊ ቋንቋ ተማሩ። ከ1914 እስከ 1916 ዓም በውጭ ጉዳይ ሚኒሲቴር ሠርተዋል።

በ1916 ዓም በታኅሣሥ ወር ወደ ፈረንሳይ አገር ሔደው በከፍተኛ የእርሻ ትምህርት ተቋም 6 ዓመት ያህል ትምህርታቸውን ከተከታተሉ በኋላ በፈረንሳይ አገር «ናሲዮናል ሱፔርዮር ዲ አግሮኖሚ ኩሎኒያል ናዦን ሱር ማርኒ ፖሪስ » ከተባለ ትልቅ

የርሻ ትምህርት ቤት በዲግሪ ተመርቀው በ1921 ዓም ወደ አገራቸው ተመለሱ።

በ1922 ዓም በቀሰሙት የርሻ ትምህርት በእምበ አውራጃ የእርሻ ልማት እንዲያከሂዱ ተደረጉ፣ ከተማውንም በመቀየስና ፕላኑን በዘመናዊ አሰራር በማዘጋጀት ሕዝቡ በታ እየተመራ ቤት እንዲሠራ ከማድረጋቸውም በላይ ባከባቢው ያለው የርሻ መሬት በዘመናዊ ዘዴ እንዲለማና የሕዝቡም ኑሮ እንዲሻሻል ስለደረጉ በስራ ትጋታቸውና በባለሙያነታቸው በዚያኑ ጊዜ ልዩልዩ ሽልማቶችን ከመንግሥት ተቀብለዋል፣በገሩም ላይ ስለሰዩት መልካም የሥራ ውጤት በሕዝቡ ዘንድ ምሥጋና አትርፈዋል።

በ1926 ዓም ወደ ወሎ ክፍለሀገር በሹመት ተዛውረው በዚያው እንዳሉ በኢጣሊያ ወራሪ ጦር ኢትዮጵያ ውስጥ ስለገባ፣ የኢጣሊያኖች ጦር አዛዥ በነበረው በግራሲያኒ ላይ የከቲት 12 1929 ዓም በተጣለው የበንብ አደጋ እሰቸውም ተጠርጥረው ከባታቸው ከፀሐፊ ትእዛዝ ወልደመስቀል ጋር ወደ ኢጣሊያ አገር ስለተወሰዱ አዚናራ በሚባል በታ ታስረው ቆይተዋል።

በ1933 ዓም ጠላት ኢትዮጵያን ከለቀቀ ወዲህ አገሪቱን እንደገና ለመገንበት በተደረገው ጥረት፣ ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደመስቀል እስከ 1938 ዓም ለወሎ ለበጌምድርና ለትግራይ ክፍለ ሀገር አስተዳደር የጽሕፈት ቤት ሹም በመሆን ከማገልገላቸውም በላይ የክፍለሀገሮች አመዳደብ መስታወት በሚል ፕላን ቻርት ሠርተው ስላቀረቡ ለገር አስተዳደር ሚኒስቴር ተሰጥቶ እሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

ከ1939 ዓም እስከ 1958 ዓም ባለው ጊዜ በልዩልዩ መሥሪያ ቤቶች በዋና ዲሬክተርነት፣በሥራ አስኪያጂነት፣ በም/ ሚኒስትርነትና በሚኒስትርነት ከሰሩ በኋላ ቀጥሎም 1958እስከ 1966 ዓም በአማካሪነት ከበድ ብሔራዊ ሐላፊነት ባለባቸው በታዎች ላይ በመሾም በፖለቲክ፣ በኢኮኖሚና በአስተዳደር ጉዳይ ታላቅ ተሰትፎ ከማድረጋቸው ጋር በአፍሪካ፣ በአውሮፖ፣ በአሜሪከና በሩቅ ምስራቅ አገሮች በዴሊጋሲዮን መሪነት፣ በአበልነትና በልዩ ልዩ ጉብኝት የስብሰበ ተከፋይ በመሆን በአገራቸው ከፍተኛ የሥራ ፍሬ አበርክተዋል።

ከዚህም በቀር የበዕድ በሕል ወረራ ኢትዮጵያን በስገበትና ወጣቱ መጥፎ ልማድ ተጋበት መበከል በጀመረበት ወቅት ከትውልድ ወደ ትውልድ ((በትውፊት)) ሲወርድ የኖረው ዓይነተኛው ያገሪቱ በህል ታሪክና ቅርስ እንዳይጠፋ በማሰብ የእረፍት ጊዚያቸውን መስዋዕት በማድረግ በየመልኩ ሰብስበውና በጽሑፍ አድርገው ለዲሱ ትውልድ ያስተላለፏቸው በተለይ « ዝክረ ነገር፤ » « ያበቶች ቅርስ፤ » « አማርኛ ቅኔና፤ » « እንቅልፍ ለምኔ » የተባሉት መጽሐፍቶቻቸው በማናቸውም ኢትዮጵያዊ ቤት ሊገኙ የሚገቡ ናቸው።

እንደዚሁም በሣይንስና በቴክኒክ የተቀነባበሩ ለእርሻ በለሙያ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የርሻን ዘዴ ጥበብና ስልት የሚያስረዱ መጽሐፍት አበትመዋል፤ እነዚህም « በዕለ ገራህትና » « ጥበበ ገራህት » የተበሉ ናቸው።

በሌለ በኩል ደግሞ ሃይማኖት ነክ የሆኑ የእግዚአብሔርን ምጥቀትና ርቀት የሚያስረዱ እንደዚሁም የፈጣሪን ሕልውና ለማወቅና መለኮትነቱን ለመመርመር የሰው ዕውቀት ፍልስፍና አለመቻሉን የሚያስገነዝቡ መጽሐፎች አበርክተዋል።

ብለቴን ጌታ ማኅተመ ሥለሴ የተፈጥሮ ትጋትና ብርታት ስለለቸው በስራቸው ለይ ሆነው ደከመኝ ልረፍ ሰይሉ ያሰተሟቸው ልዩ ልዩ መጽሐፍቶች 16 ያሀል ሲሆኑ በስነ ጽሑፍ በኩል ለበረከቱት እስተዋጽእ በ1958 ዓም ከፍተኛ ሽልማት ተቀብለዋል።

ብለቴን ጌታ ማኅተመ ሥለሴ በመንግስት ቁጥጥር ስር እንዳሉ በጋጠማቸው ድንገተኛ ሕመም ምክንያት፤በመንግስት ፈቃድ በሐኪም እንዲረዱ ከተደረገ በኋለ እግዚአብሔር የወሰነውን ቀን ማስፍ ስለማይቻል ጥቅምት 8 ቀን 1971 ዓም በ74 አመት ዕድሜያቸው እርፈው አስከሬናቸው ከሆስፒታል ወደ ቤታቸው ተወስደ ጥቅምት 9ቀን 1971 ዓም ልጆቻቸውና.ዘመድ ወዳጅ በተሰበሰበበት በየከ ቅዱስ ሚከኤል ቤተ ክርስቲያን የኑሮ ጓደኛቸው የወይዘሮ እምሣለወርቅ ከፈተው አሥከሬን በረፈበት ራስቸው በሣነጹት የመቃብር ስፍራ የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት በክብር ተፈጽሟል።

ብለቴን ጌታ ማኅተመ ሥለሴ ወልደመሥቀል 74ኛው ዓመት

የልደታቸው ዘመን በሚታሰብበት ዕለት ለጥቅምት 19 ቀን 1971 ዓም እንዲሰማ፣ በማስታወሽ ጽፈውት የተገኘው ቃል ቀጥሎ ያለው ነው፤

አቀርባለሁ ለምለክ ልቢዊ ምሥጋና፣
አድርሰኛል ከዚሕ ለጥቶ ሙሉ ጤና።
ያደረግሁት ጉዘ የረዘመ ነው፣
ደከሞኛል ታክቶኛል ቢበቃኝ ምነው።
ከእንግዲህስ ወዲያ ልረፍ እባክህ፣
ይሁን ብለህ እዘዝ ባለስልጣን ነህ።

ማ. ሥ

እንደተመኙትም ልመናቸው ከፈጣሪያቸው ዘንድ ደርሰ ጥቅምት 8 1971 ዓም አረፉ።

ብለቴን ጌታ ማኅተመ ሥለሴ ወልደ መሥቀል አበታቸው ፀሐፊ ትእዛዝ ወልደመሥቀል በተናገሩት ቃል ለንተ ለልጄ የንሥሐ አበትህ እኔው አባትህ ነኝ በሚለው አበታዊ ምክርና ምርቃት በመደገፍ መንፈሰዊ ሥራዎችን የሚያዘወትሩ እግዚአብሔርን ፈሪና ሰውን አክብረው ሥራን የሚያመልኩ ዕረፍትን የማያውቁና ሕይወታቸው ትጋትና ብርታት የተመለበት መልከም ሰው ነበሩ።

ከቃል ኪዳን ባለቤታቸው ከወይዘሮ እምሣለወርቅ ከፈተው ሰባት ወንደችና እራት ሴቶች ልጀች ወልደው የልጅ ልጅ አይተዋል።

በፈተና የሚፀና ሰው የተባረከ ነው፣ ከተፈተነ በኃላ ለሚወዱት ተስፋ ሰለእርሱ የሰጣቸውን የሕይወት አክሊል ይቀበሰልና።
የያዕቆብ መልዕክት ም.፩ ቁጥር ፲፪

## የብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደመስቀል

### የሕይወት ታሪክ ማስታወሻ።

1) ከተወለድኩ ከ40 ቀን በኋላ 7 ዓመት እስኪሞላኝ ድረስ ወይን አምባ ቡልጋ አደግሁ። የአማርኛ ትምህርት ማጥናት የጀመርኩት እዚያው ነው።7ኛ አመቴ ሲያልቅ አዲስ አበበ መጣሁ።የአማርኛ ትምህርቴን በልዩ አስተማሪ ከቤት እንደሆንኩ ቀጠልኩ።

-- ከ1904-1913 ዓም አዲስ አበበ ቅድስት ሥላሴ የኔታ ኃይለ ሥላሴ ዘንድ አዳሪ ሆኜ የአማርኛ ትምህርት ቀጠልኩ።

ከ1907-1913 ዓም በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት የፈረንሳዊ ቋንቋ ስማር ቆየሁ።

--ከ1914-1916 ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አገለገልሁ፣

-በኅዳር 1915 ዓም ከወይዘሮ እምሣለወርቅ ከፈተው ጋር ተጋበን።

--በ1915 ዓም አበቴን ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀልን ተከትዬ ኤደንን /የእንግሊዝ ፕሮቴክትራ/ ጎበኘሁ።

--በታኅሣሥ 13 ቀን 1916 ዓም ለትምህርት ወደ ውጭ አገር ሄድኩ። /ግን እናቴና ባለቤቴ ሳያውቁ ተደብቄ ነው።/

--መጀመሪያ ከሚሲዮን ለይክ ሊሴ ፍራንሴ ተማሪ ቤት ካይሮ (MISSION LAIQUE FRANCAISE LYCE DU CAIRE) ገባሁ። ከአንድ ዓመት በኋላ ተስማሚ አየር በመፈለግ ወደ ፈረንሳይ አገር ባስ ፒረኒ (basse pyrenees) ተዛወርኩ።እዚያ ከሌጅ እንዳለሁ ለሁለት ዓመት የርሻ ትምህርት አጠናሁ።

--በመጨረሻ እንስቲቱት ናሲዮናል ሱፒርየር ደ አግሮኖሚ ኮሎኒያል ኖዥን ሱር ማርን ፖሪስ (Institut National Superiour D'Agronomie (Nogent sur Marne Paris) ከሚባል ትልቅ የእርሻ ትምህርት ቤት ገብቼ ትምህርቴን አጠናቀቅሁ።

2) በነሐሴ 24 ቀን በ1921 ዓም ትምህርቴን ጨርሼ ወደ አገሬ ተመለስኩ።
3) በመጋቢት 1 ቀን 1922 ዓም እምበን እንደቀና ታዝዤ ሥራ ጀመርኩ።
4) በ1922 ዓም ስለእርሻ ትምህርቴ የዳግማዊ ምኒልክን የወርቅ ሜዳይ ተሸለምኩ።
5) በጥቅምት 1923 ዓም በግርማዊ ን ነ ቀ ኃይለ ሥለሴ የንግሥት በዓል ለይ እምበል የሌለውን የሥለሴ ልሽን ተሸለምኩ።
6) በኀዳር 1926 ዓም የእምበን ሥራ ስስመርቅ ባለእምበል የሥለሴን ልሽን ተሸለምኩ።
7) በነሐሴ 16 ቀን 1926 ዓም ባለምባራስ ተብየ የልዑል አልጋ ወራሽ እስፋ ወሰን ኃ ሥ የጽሕፈት ሹም ተባልኩ።
8) በየካቲት በ1929 ዓም በግራሲያኒ አደጋ ምክኒያት ታስሬ ኢጣሊያ አገር ሄድኩ።
9) በነሐሴ 24 ቀን 1930 ዓም ከታሰርኩበት ተፈትቸ አዲስ አበባ ገባሁ። መጋቢት 1933 ዓም፤ ግርማዊነታቸው በጎጃም በኩል ወደ ኢትዮጵያ በሚመጡበት ጊዜ ተጠርቸ ደብረ ማርቆስ በዓይርፕለን ሄድኩ።
10) ከግንበት 1933 ዓም እስከሚዚያ 1938 የወሎ የበጌምድርና የትግሬ ጠቅለይ ጽሕፈት ቤት ሹም ሆንኩ።
11) በነሐሴ 25 ቀን 1938 ዓም የእርሻ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ሆንኩ።
12) ከ1940-1941 በተለይ የቆመ የርሻና የከብት ርቢ መሥሪያ ቤት ሥራ እስኪያጂ ሆንሁ።
13) በሰኔ 25 ቀን 1941 ዓም የርሻ ምክትል ሚኒስቴር ተባልኩ።
14) በግንበት 8 ቀን 1942 ዓም ከውጭ አገር ሰደተኞች ለማምጣት ወደ አውሮፖ /ጀርመን/ ተለክሁ።
15)በሚያዚያ 27 ቀን 1943 ዓም የኢትዮጵያን የክብር ከከብ ልሽን ያንገት ከነፐለኩ ተሸለምኩ።
16) በጥቅምት 1 ቀን 1945 ዓም ስለጦር ከሣ ጉዳይ ወደኢጣሊያ አገር

የዴሊጋሲዮን አባል ሆኜ ሄድኩ።
17) በሰኔ 30 ቀን 1945 ዓም የአዲስ አበባ ከተማን በተጠባባቂ ከንቲባነት እንድሠራ ታዘዝኩ/የርሸ ም ሚኒስትርነቴን እንደያዝኩ/
18) በሚያዚያ 9ቀን 1946 ዓም የአርሸ ሚኒስቴር ተባልኩ።
19) በሰኔ 21 ቀን 1947 ዓም አበቴ ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደመስቀል ስለሞቱ ከትልቅ ሐዘን ላይ ወደቅሁ።
20) በሐምሌ 2 ቀን 1947 ዓም የጀርመን መንግሥት ጋብዞኝ ለጉብኝት ወደ አውሮፖ ሄድኩ።
21) በሐምሌ ወር 1947 ዓም ከጀርመን መንግስት ባለክርደን ልሽን ተሸለምኩ፤
22)በጥቅምት 22 ቀን 1947 ዓም የኢትዮጵያ ክብር ኮከብ ልሽን ባለ ክርደን ተሸለምኩ።
23) በግንቦት 11 ቀን 1948 ዓም የአሜሪከን መንግሥት ጋብዞኝ ወደ አሜሪከን ሄድኩ።
24) በ1948 ዓም የዩጎስለቪያን ባለ ክርደን ኒሽን ተሸለምኩ።
25) በ1948 ዓም ከግሪክ መንግሥት ታለቅ ክርደን ክርደን ደሰንጀርጅ ተሸለምኩ።
26) በ1948 ዓም የሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴርን በተጠባባቂነት ለጥቂት ወራት መራሁ።
27) በ1948 ዓም ከቸኰዝሎቨኪያ መንግሥት ታለቅ/ ክርደን እርደር ዲሊዮን ብላፕ/ ተሸለምኩ።
28) በመጋቢት 23 ቀን በ1950 ዓም የገንዘብ ሚኒስቴርን ተሾምኩ።
29) በሐምሌ 15 ቀን 1953 ዓም የትምህርት ሚኒስቴር ደኤታ ተባልኩ። በዚያን ጊዜ ሚኒስቴሩ በንጉሠ ነገስቱ ስም ይመራ ነበር።
30) የከቲት 1 ቀን 1953 ዓም የሥራና መገናኛ ሚኒስትር ተባልኩ።
31)በየከቲት 14 ቀን 1953 ዓም የዳግማዊ ሚኒልክን ታለቅ መከንን ተሸለምኩ።
32) በሐምሌ 28 ቀን 1953 ዓም ስለአይሮፕለን ማሰረፍ ውል ጉዳይ ወደ

ግሪክ አገር ለንግግር ሄድኩ።

33) በጥቅምት 9 ቀን 1954 ዓም (ለአያታ) ከንፈራንስ ሲድኒ /አውስትራሊያ/ ሄድኩ። ከዚያም በሆኖሉሉ በኩል አድርጌ አሜሪካና ካናዳ ደርሼ 48,000 ኪሎ ሜትር ከደረስኩ በኃላ አዲስ አበባ ተመለስኩ።

34) ጳጒሜ2 ቀን 1954 ዓም ለአያታ ከንፈረንስ ወደ ዱብሊን ኢርላንድ ከጌጤነሽ ማኅተመ ሥላሴ ጋር ሄድኩ።

35) በጥር 8 ቀን 1955 ዓም ማድሪድ ለይ በሚደረገው የመስመር መክፈት ምረቃ ሥነ ሥርዓት ለመገኘት የደሊጋሲዮን መሪ ሆኜ በጄት አውሮፕላን ሄድኩ። ልጅ ለይፋና ወይዘሮ ሰፍያም ከኔው ጋር መጥተው ነበር።

36) በጥር 20 ቀን 1955 ዓም ለአውራ ጎዳና ሥራ ከዓለም ባንክ ገንዘብ ለመበደር የዴሊጋሲዮን መሪ ሆኜ ወደ ዋሽንግተን ሄድኩ። ስመለስ ሐረገወይን ማኅተመ ሥላሴ ከኔው ጋር መጣች።

37) በግንቦት 22 ቀን 1956 ዓም ከወይዘሮ እምሰለወርቅ ክፈተው ጋር ለሕክምና ወደ ሃምቡርግ/ጀርመን/ ሄድን፤በሰኔ 10 ቀን 1956 ዓም ወይዘሮ እምሰለወርቅ አፕራሲዮን ሆነች። ከኛም ጋር ሐረገወይን ማኅተመ ሥላሴና ታሪኩ ማኅተመ ሥላሴ ነበሩ።

38) በኅዳር 6 ቀን 1957 ዓም ለምስራቅ ኦርቶዶክስ ፖትርያርክች የጃንሆይን የግብዣ ደብዳቤ ለማድረስ ተልኬ ሄድኩ። የደረስኩባቸው አገሮች ግብጽ፣ ግሪክ፣ ሌባኖስ፣ ሰሪያ፣ ቱርክ፣ ቆጵሮስ፣ ጆርዳንና እስራኤል ናቸው። በዚሁም አጋጣሚ ወይዘሮ እምሰለወርቅ ክፈተውና በለጠ መኅተመ ሥላሴ ቢይሩት ድረስ መጥተው በአንድነት እየሩሳሌምን ተሳለምን።

39) በመስከረም 15 ቀን 1958 ዓም በስነ ጽሑፍ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ተቀበልኩ።በበአሉ ለይ የህንድ ፕሬዚዳንም ነበሩ

40) በሚያዚያ 10 ቀን 1958 ዓም ብላቴን ጌታ ተብየ የዘውድ እማከሪነት ተሾምኩ።

41) በሚያዝያ 10 ቀን 1958 ዓም ወደ ቶክዮ ጃፖን አገር ለመጎብኘት ሄድኩ። ወደ ጃፖን ከመጓዜ አስቀድሞ አውሮፖ ሄጄ ነበርና የተነሳሁት ከሎንደን ነው። በዚሁ አጋጣሚ ጊዜ የተዘዋወርኩባቸው አገሮች ጠቅላላ የመንገድ ሬዝመት 41 187ኪሎ ሜትር ሆኗል።

42) በኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር ስም ሆኘ ዩጎዝለቪያ ለመገኘት በነሐሴ 17 ቀን 1959 ዓም ከአዲስ አበባ ተነሳሁ። በዚሁም አጋጣሚ ሆንገሪን፣ኦትሪሽንና ቼከስሎቨኪያን ከጎበኘሁ በኋላ በጳጉሜ 5 ቀን 1959 ዓም አዲስ አበባ ተመለስኩ።

43) በጥቅምት 28 ቀን 1960 ዓም የግርማዊ ቀ ኃ ሥ መልክተኛ በመሆን ለኢራኑ ሻህ (ንጉሥ ነገሥት) የንግስ በዓል ስጦታ ለማድረስ ከአዲስ አበባ ተነሳሁ።

44) ከግንቦት 18 ቀን 1962 ዓም እስከ ሐምሌ 5ቀን 1962 ዓም ዩጎስላቪያና ነምሳ (ለድጋስታይን) ሄጄ አገር ጎበኘሁ።

45) ከጥቅምት 13 ቀን 1963 ዓም እስከ ኅዳር 14 ቀን 1963 ዓም እሥራኤል (ኢየሩሳሌም)ከልጄ ሚሊዮን ጋር ሄጄ አንገቴን አፐራሲዮን ሆኜ ተመለስኩ።

46) በሐምሌ 16 ቀን 1964 ዓም የዳግማዊ ምኒልክን ታላቅ ክርደን ተሸለምኩ። በኅዳር 16 ቀን 1965 ዓም የጋብቻችንን የወርቅ ኢዮቤልዩ 50 ዓመት የከ ለይ አከበርን።

47) ከየካቲት 14 ቀን እስከ የካቲት 24 ቀን 1965 ዓም በኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋበዥነት፣ ሸንግሐይንና ፔኪንግን ጎብኝቼ ተመለስኩ።

48) ከመጋቢት 6 ቀን 1965 እስከ መጋቢት 14 ቀን 1965 ዓም ልዑል እልጋ ወራሽ መርድ አዝማች አስፋ ወሰን ኃይለ ሥለሴን ለመጠየቅ ሎንደን ሄድኩ።

49) ከግንቦት 6 ቀን እስከ ሰኔ 15 ቀን 1965 ዓም ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ጋር ሰሜን አሜሪከንን፣ ዌስት ኢንዲስን፣ ስዌስንና እሥራኤልን ኢየሩሳሌምን ጎብኝቸ ተመለስኩ። በዚሁ ጊዜ

የተዘዋወርነው የመንገድ ርቀት 41,545 ኪሎ ሜትር ሆኗል።

50) በታኅሣሥ 11 ቀን 1966 የብሔራዊ መርሐ ልሳን /አካዳሚ/ ፕሬዚዳንት ተባልኩ።

II. በያይነቱ ዲፕሎሞች/ የምስክር ወረቀቶች/ የሹመት ደብዳቤዎችና በየጊዜው ስለሥራ ጉዳይ የተፃፉ ማዘዣዎች /ዶሲየውን ተመልከት/

III. ስለአገር ውስጥ አስተዳደር በየጊዜው የተፃፉ ራፖሮች /ስለሥራ እንቅስቃሴ/

ሀ/ ስለ ወሎ ጠቅላይ ግዛት

ለ/ ስለ ትግራይ ጠቅላይ ግዛት

ሐ/ ስለ በጌምድርና ሰሜን ጠቅላይ ግዛት

IV በበላይ ስለማስተዳድራቸው መስሪያ ቤቶች እንቅስቃሴ በየጊዜው ለመንግሥት ያቀረብኳቸው ራፖሮች

1. በተለይ ስለቆመው የርሻና ከብት ርቢ፣
2. ስለእርሻ ሚኒስቴር
3. ስለ ማዘጋጃ ቤት /በተጠባባቂነቴ ጊዜ/
4. ስለ ገንዘብ ሚኒስቴር
5. ስለ ትምህርት ሚኒስቴር
6. ሥለ ሥራናመገናኛ ሚኒስቴር
   ሀ/ ስለ አውራ ጎዳና
   ለ/ ስለ አየር መንገድ
7. ልዩ ልዩ ራፖሮች/ ስለ ልዩ ልዩ መሥሪያ ቤቶች/

V. በውጭ አገር ስለተደረጉ መልእክቶች ራፖር፣

ሰፋ ያለ ስለሆነ ዝርዝሩን ከደሲየው መመልከት ነው።

VI. በውጭ አገር ስለተደረጉ ጉብኝቶች ራፖር፣

ሰፋ ያለ ስለሆነ ዝርዝሩን ከደሲየው መመልከት ነው።

VII. በልዩ ልዩ ምክንያት እስከ 1958 ዓም የተደረጉ ንግግሮች /ዲስኩሮች/

1 በርሻ ሚኒስቴር የተደረጉ ዲስኩሮች/ደስየውን ተመልከት/

2 በገንዘብ ሚኒስቴር የተደረጉ ዲስኩሮች/ደሲየውን ተመልከት/

3 በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒሲቴር የተደረጉ ዲስኩሮች /ደሲየውን ተመልከት/

4 በሥራና በመገናኛ ሚኒስቴር የተደረጉ ዲስኩሮች/ ደሲየውን ተመልከት/

5 በልዩ ልዩ ክፍል የተደረጉ ዲስኩሮች/ደስየውን ተመልከት/

VIII. የየበርዱና የየኮሚቴው አባል ወይም ፕሬዚደንት በመሆን በግርማዊነታቸው ትእዛዝ ካገለገልኩባቸው የሥራ ክፍሎች ዋና ዋናዎቹ

1. የእህል ድርጅት በርድ አባል........ ..... ...... ....... በ1942 ዓም
2. የስደተኛ መጠባበቂያ ድርጅት ኮሚቴ ም/ ፕሬዚደንት...... በ1942 ዓም
3. የ1944ዓም ኤክስፖሲዮን አዘጋጅ ኮሚቴ አባል......... ..በ1944 ዓም
4. በርሻ ሚኒስቴር የርሻ ምክር ቤት ፕሬዚደንት ...............በ1946 ዓም
5. የኢት መንግሥት የልማት ዲቬሎፕሜንት ባንክ ፕሬዚደንት ...............በ1946 ዓም
6. የግርማዊ ን ነ እና የግርማዊት እቴጌ 25ኛው ዓመት በኢዮቤልዩ የዘውድ በዓል ዝግጅት አደራጅ ኮሚቴ........... በ1947 ዓም

7. የሀገርና የሕዝብ ኢኮኖሚ ምክር ቤት አባል.............በ1947 ዓም
8. የ1948 ኤክስፖዚሲዮን አዘጋጅ ኮሚቴ አባል............ በ1948 ዓም
9. የወጣቶች ወንዶች ክርስቲያናዊ ማኅበር ፕሬዚዳንት ...............በ1948 ዓም
10. የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል የዲሬክተሮች ቦርድ ፕሬዚዳንት .........በ1949 ዓም
11. በሐረር የዓለም ማያ የእርሻ ኮሌጂ ባለ አደራ ቦርድ ፕሬዚዳንት ........ በ1949 ዓም
12. የልዑል መኰንን ኃ ሥ መታሰቢያ ድርጅት ቦርድ አባልና ም/ አቃቤ ነዋይ ....... በ1950 ዓም
13. የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ የዲሬክተሮች ቦርድ ም/ ፕሬዚዳንት .........በ1950 ዓም
14. የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ አቋም የሚሻሻልበት አዋጅና ሌሎች ባንኮች የሚቋቋሙበት ደንብ በሰብሳቢነት .............. በ1951 ዓም
15. የአዲስ አበባ ከተማ ልማት አጥኝ ኮሚቴ አባል ..............በ1951 ዓም
16. የቴክኒክና የኢኮኖሚ እርዳታዎች ቦርድ አባል........... በ1951 ዓም
17. በግርማዊነታቸው ሰብሰቢነት የፕላኒንግ ቦርድ አባል ..............በ1951 ዓም
18. የትምህርት ቦርድ አባል ... በ1952 ዓም
19. የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድርጅት ፕሬዚዳንት ... በ1953 ዓም
20. የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቦርድ አባል ...በ1953 ዓም
21. የነዳጅ ዋጋ አወሳሰን ኮሚቴ አባል ...በ1953 ዓም
22. ስለ ኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት አስተዳደር ልዩ ኮሚቴ አባል ...በ1953 ዓም
23. የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቦርድ ፕሬዚዳንት ... በ1953 ዓም
24. የአውራ ጎዳና ባለስልጣን ፕሬዚዳንት ... በ1953 ዓም
25. የቅድስት ሥላሴ የመንፈሳዊ ትምህርት ቤት አስተዳደር ኮሚቴ አባል ... በ1953 ዓም
26. የወበ ማጥሬያ ቦርድ አባል ... በ1954 ዓም

27. የመንግሥት መረዎች አቀባበል ድርጅት የበላይ ኮሚቴ አባል ... በ1954 ዓም
28. የናዝሬት ዲስ የምድር ባቡር መስመር ጥናት ማኅበር ፕሬዚዳንት ... በ1954 ዓም
29. የአሰብ የነዳጅ ማጣሪያ በርድ አባል ... በ1956 ዓም
30. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲን አስተዳደር በርድ አባል ... በ1955 ዓም
31. የሲቪል አቪያሲዮን በርድ ሊቀ መንበር ... በ1955 ዓም
32. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የዲሬክተሮች በርድ አባል ... በ1956 ዓም
33. የስፍት ድሪንክ በርድ ፕሬዚዳንት /በድሬዳዋ/ ... በ1956 ዓም

34. በጠቅላይ ሚኒስትሩ ስብሰቢነት የፐላኒንግ በርድ አባል
35. የከከ ከሰ በርድ ፕሬዚዳንት /አዲስ አበባ/
36. የትምባሆ ሞኖፖል በርድ ፕሬዚዳንት
37. የአሲስታንስ ኢከኖሚክ በርድ ፕሬዚዳንት
38. የኢትዮጵያ ኢንስቲቱዩት ፖስተር በርድ አባል
39. የፋዎ ኮሚቴ ሰብሰቢ
40. የመጀመሪያው የ5 ዓመት ፐላን ጥናት በርድ
41. የሥራ ተቋራጮች ከስራና መገናኛ ሚኒስቴር ጋር ስለሳቸው ውዝፍ ሂሣብ አጣሪና ወሰኝ ኮሚቴ ሰብሳቢ
42. የኢትዮጵያን ምድር በቀለድ ስለመለከት የተቋቋመው ኮሚቴ ፕሬዚዳንት

<u>በየጊዜው ያስተምኪቸውና ያዘጋጇኂቸው መፃሕፍት</u>

<u>አንደኛ ክፍል፤ ታሪክና ባህል</u>

1 <u>ዝክረ ነገር</u>፣ /ሁለት ጊዜ ታትሟል/ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት በ1962 ዓም

2 <u>ያበቶች ቀርስ</u>፣ /ሦስት ጊዜ ታትሟል/ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት

በ1961 ዓም ነፃነት ማተሚያ ቤት 1943 ዓም

3 እንቅልፍ ለምኔ፣ /ሦስት ጊዜ ታትሟል/ በኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት 1952 ዓም

4 አማርኛ ቅኔ ነጠሰ፣ /አምስት ጊዜ ታትሟል/ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1957 ዓም

5 አማርኛ ቅኔ ከነመፍቻው፣ /ሦስት ጊዜ ታትሟል/ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1961 ዓም

6 ስለኢትዮጵያ የመሬት ሥሪት አስተዳደርና ግብር፣ በታይፐ ተጽፎ የተጠረዘ 1949 ዓም

7 ያገር በህል ቡልጋ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1959 ዓም

8 ባለን እንወቅበት፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1958 ዓም

9 የቀድሞ ዘመን ጨዋ ኢትዮጵያዊ ጠባይና በህል፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1958 ዓም

10 ቼ በለው፣ ንግድ ማተሚያ ቤት 1961 ዓም

11 ጉልቁ ትውልድ ዘንጉሥ ኃህለ ሥለሴ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1965 ዓም

12 የኛም አሉ እንወቃቸው፣ በታይፐ፣ ጥር 1958 ዓም

ሁለተኛ ክፍል፣ ትምህርተ ጥበበት

13 ጥበበ ገራህት፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1944 ዓም

14 ብዕለ ገራህት፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1959 ዓም

ሦስተኛ ክፍል፣ እንክሮ ለእግዚአብሔር ወተዘክሮ ለነፍስ መንፈሳዊ/

15 ዕፁብ ድንቅ፣ ነፃነት ማተሚያ ቤት 1943 ዓም

16 ስም ከመቃብር በላይ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1956 ዓም

17 ሰዋሰወ ሰማይ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1961 ዓም

## «ኢትዮጵያ» የሚለው ቃል እውነተኛ ትርጉም፤

ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? ከወዴትስ የመጣ ቃል ነው? በታሪክ ቃሉ የተመዘገበው ከመቼ ጀምሮ ነው? ወዘተ የሚሉት ጥያቄዎች በየጊዜው ሲነሱና ብዙዎችን ሲያከራክሩ ይገኛሉ።

የሚሰጡት መልሶች ግን አጥጋቢ አይደሉም፤ እንዲያውም አልፎ አልፎ ጥራዝ ነጠቅና የተዛባ፣ የተሳሳተም መልስ ሲሰጥ እንሰማለን። ይህንን ለማረምና ለማስተካከል በማለትም የሚቀጥለውን ጽሑፍ ለመጻፍ፣ ተያይዞ የቀረበውንም « ኔግሮ ኒገር» (NEGRO; NIGGER) የሚሉትን ቃላት አመጣጥ ለመመርመር ምንጫቸውንም ለማግኘት ተነሳን።

ጥራዝ ነጠቅ ብለን የምንቆጥረው ትንተና (ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ETHIOP ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ነው፤ ትርጉሙም ጥቁር ቆዳ ያለው ማለት ነው።» የሚለውን፣ ወይንም ተመሳሳይ ጥልቀት የሌለውን ገለፃ ነው። በግሪክ ሥነ ጽሑፍ ብንመለከት ዓይነ ስውሩ ሆመር በተረከው የኢልያድና የኦዲሲ ታሪክ እየደጋገመ፤

« ዜውስ የተበለው የአማልክት ጌታ ወደ እግዚአብሔር ፈሪዎች አገር ወደ ኢትዮጵያ ሲሄድ በታላቅ አቀባበልና በብዙ የፍሪዳዎች መስዋዕት ይቀበሉታል» እያለ በማድነቅና በማጋነን ተናግሩዋል። ይህ የሆነው ግን በታሪክ አምድ ዘመኑ አጭር ነው። የግሪክ ስልጣኔ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰው በአምስተኛውና በስድስተኛው መቶ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት ሲሆን ከዚያ ቀደም ብለን አንድ ወይንም ሁለት ሺህ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት ብንመለከት ግን የግሪክ ስልጣኔ ሆነ የግሪክ ቋንቋ ገና በታሪክ ገጽ ያልተለመደ ሆኖ እናገኘዋለን።

የዚሁ ዓይነት ተመሳሳይ ጥራዝ ነጠቅ ትንተናም (NEGRO;

NIGGER) ኔግሮ የሚለው ቃል የተገኘው ከላቲን ኔግራ (NEGRA) ከሚለው ቃል ሲሆን ትርጉሙም ጥቁር ማለት ነው የሚለውን ዓይነት ነው። እንግዲያውስ ባደረግነው ምርምር ከእነዚህ ጠለቅ ያለ አመለካከት አለው ብለን የምናምንበት ገለፃ ከዚህ ቀጥለን እናቀርባለን።

ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ በጹሑፍ የምናገኘው በመጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን ይኸውም ሙሴ ኢትዮጵያዊት ሴት ሚስት በማግባቱ ወንድሙ አሮንና እህቱ ማሪያም እንደተማሉት የሚዘረዝረው ታሪክ ላይ ነው (ኦሪት ዘሁልቅ 12 1) እንግዲያውስ በታሪክ ቆጠራ ግምት የእሥራኤል ልጆች ከግብጽ አገር በሙሴ መሪነት የወጡበት ዘመን ከሺህ አምስት መቶ እስከ ሁለት ሺህ ዘመን ከክርስቶስ በፊት እንደሆነ ይገመታል። ታዲያ ይህ ሙሴ ለሚስትነት ያገባት ሴት «ኢትዮጵያዊት» ተብላ ከተጠራች ኢትዮጵያዊነት በመልክ፣ በቋንቋ፣ በባህል፣ እንዲሁም በመሳሰለት መለዮዎች የሚታወቅ ዘርና ሕዝብ ሆኖ ከዚያ በፊት ለብዙ ዘመናት መቆየቱ አያጠራጥርም።

(በነገራችን ላይ ይኸ የባእድ ሚስት አገባህ ተብሎ በቤተሰብ ውስጥ የሚነሳው ችግር ከጥንት የቆየ ጉዳይ ይመስላል።)

አንዳንድ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያ ብሎ ሲጠቀስ የሆነ ሌላ አገር እንጂ የአሁኑን ኢትዮጵያ አይደለም፣ ወደ የመንና ወደ ዓረብ አገር በኩል ያለ ሌላ አገር ነበር የሚሉ አሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ስንመረምር ኢትዮጵያ የሚለው ስለዓረቦች ሳይሆን ስለ ጥቁር ሕዝብ መሆኑን መረጃ በትንቢተ ኤርምያስ 13:23 ብንመለከት «...ኢትዮጵያዊ ሰው ጥቁረቱን፣ ነብር የቆዳውን ጠቃጠቆ ሊለውጥ ይቻለዋልን?» ይላል።

የታሪክ መጽሐፎችን ብንመለከት ደግሞ ክብረ ነገሥትና በአለቃ ታየ ገብረ ማሪያም መጽሐፍ በኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ተጠቅሶ የሚገኘው ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ኢትዮጲስ ከሚባለው ንጉሥ ስም ተያይዞ ሃገሩም በንጉሡ ተሰየመ፣ ኢትዮጵያም ተባለ ብሎ ያስረዳል። (<u>የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ</u> ገጽ 20) ታሪኩም

ሲዘረዝር ኢትዮጲስ የሰበ አበት፣ የአክሁናስ የልጅ ልጅ ነው ፤ አምስት ልጆችም ነበሩት፤ ስማቸውም ሳክንዱ፣ ኖበ፣ ሰበ፣ በለው፣ ከለው ይባላሉ። ከእነዚህ ታላቁ ሳክንዱ የአባቱን የኢትዮጲስን ዙፋን ሲወርስ ሌሎቹ በዙሪያው የነበሩትን አገሮች ይገዙ እንደነበር ያስረዳል።

ይኸ ሁሉ የቅዱሳት መጽሐፍትና የሃገር ቋሚ ጽሑፍ ታሪክ እያለ ታዲያ ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ከግሪክ ተገኘ ማለት የፊቱን ወደ ኋላ የኋላውን ወደፊት ማዟዟር ስለሆንብን ነው ጥራዝ ነጠቅ ብለን ያልነው። ምን አልባት የኢትዮጵያ ሰዎች ወደ ግሪክ አገር በጥንት ዘመን ሄደው ስነዉ ሕዝብ ጥቁር ማየቱ ብርቅ ሆኖበት፣ ጥቁር ቆዳ በኢትዮጵያዊያን ለመጀመሪያ ጊዜ በማየቱ ETHIOP የሚለውን ቃል ጥቁር ቆዳ ስላለ ቃሉ ከግሪኮች የመጣ ቃል ነው ሊባል አይገባም።

ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ትርጉም ምን ማለት ነው? ኢትዮጲስ የሚባለው ንጉሥ ለምን ይህን ስም ተሰጠው ብለን በጠየቅንበት ጊዜ ያገኘነው መልስ ለእኛም በቋንቋችን ማስረጃ ስላላገኘንበት አጥጋቢ ሆኖ አላገኘነውም፤ይሁንና አበቶቻችን ኢትዮጵያ የሚባል መልክም መዓዛ ያለው የዕጣን ስም ነው ይላሉ።ይኸንን እንግዲያውስ ቋንቋ የሚመረምሩ (Linguists) እንዲያተኩሩበት በዚሁ እንተወዋለን።

ወደ ሁለተኛው ምርምር ብንመለስ፣ ኔግሮ፣ ኒገር (NEGRO NIGER) የሚሉ ቃላት የመጡት ኔግራ (NEGRA)፣ ትርጉሙም ጥቁር ማለት ከሆነው ከላቲን ቃል የመጣ አይደለም። ቃሉስ የተገኘው በአፍሪካ በርዝመቱ ሦሥተኛ ከሆነው ናይጀር ከተባለው ወንዝ የተገኘ ነው። ይኸ ወንዝ ጊኒ (GUINEA) ከተባለች የምዕራብ አፍሪካ ሃገር ተነስቶ አምስት ሃገሮችን አቋርጦ ወደ አትላንቲክ ውቂያኖስ ይፈሰል። ከሚያቋርጣቸው ሃገሮች ሁለቱ ኒጀርና ናይጀሪያ ተብለው በወንዙ ስም ተጠርተዋል። እንግዲያውስ ይኸ ወንዝ በቁመቱ ሦሥተኛ ቢሆንም እንኳን አቋርጧቸው በሚያልፍ

ሃገሮች ብዛት አንደኛ ነው። ረዥሙ የአፍሪካ አንደኛ ወንዝ ዓባይ፣ (NILE) ነጭ ዓባይ ከኡጋንዳ ተነስቶ በሱዳንና በግብጽ አልፎ ወደ መከከለኛ ባሕር (MEDITERANIAN) ሲፈስስ ጥቁር ዓባይ ደግሞ ከኢትዮጵያ ተነስቶ በሱዳንና በግብጽ አቋርጦ ወደ ባሕር ይፈስሳል። ይኸውም ማለት በሦሥት ሃገሮች ብቻ ያልፋል ማለት ነው።

የናይጀር ወንዝ የሚበዛውን ርዝመቱ ማሊ (MALI) በተባለው ሃገር ይገዛል። ማሊ ከጥንታዊያን የአፍሪካ ሃገሮች አንዷ ስትሆን ብዙ የቆየ ታሪክ ያለትና ከፍተኛ የጥበብና የስልጣኔ መደብር እንደነበረች ይነገራል።እንግዲያውስ በምርምር (RESEARCH) እንደአገኘነው ናይጀር የሚለው ቃል ከማሊ ቋንቋ ተገኝቶ ለወንዙም ስም እንደወጣለት ነው፣ እንጂ ከላቲን አምጥቶ ወደ አፍሪካ ወንዝና አህጉሮች ኔግራ (NEGRA) ከሚለው ቃል ጥቁር እያሉ ስም አልወጣም። ምንአልባት ግን ከናይጀሪያ ወይንም ኒጀር ከተባለው ሃገር ወደ ኢውሮጳ ጥንት ሰዎች ሄደው ለነጩ ሕዝብ ሲታዩ የመጀመሪያ ጥቁሮች በመሆናቸው ኔግራ የሚለው ቃል ጥቁር ተብሎ ወደ ለቲን ቋንቋ ለመግበቱ ምክኒያት እንደሆነ ይገመታል።

በሃገራችን የዚሁ ዓይነት የቃላት መዘዝር ብንመለከት በሪያ፣ ሸንቅላ የሚሉትን እናገኛለን። በሪያ ጥንታዊ ቃሉ በገንዘብ የተገዛ የቤት አገልጋይና አሽከር ማለት ሳይሆን በኤርትራ ክፍለ ሃገር ኩናማ ከሚባለው ጎሳ አጠገብ የሚኖር ሌላ ጎሳ ነው። ታዲያ ከትግሬ ደጋው ወገን እየዘመቱ በመማረክ ወስደው የበሪያን ሰዎች አሽከርና የቤት አገልጋይ ይደረግ ስለነበረ ቃሉ ከዚያው ተወስዶ በሪያ ማለት በገንዘብ የሚሸጥ የአገልጋይ መልክ ይዞ በቋንቋው ረጋ። ሸንቅላ የሚለውም ተመሳሳይ ታሪክ አለው፣ ግን የሸንቅላ ጎሳ የሚገኘው ከወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በሱዳን ጠረፍ ከሚጠጉት ክፍለ ሃገሮች ነው።

ኔግሮ፣ ኒገር (NEGRO: NIGGER) ወደ አሚሲቸው ቃላት ተመልሰን የማሊን ሃገር ሰዎች ጠይቀን እንደተረዳነው ናይጀር የተባለው ወንዝ በዓሣ አጥማጆች የታወቀ ስለሆነ፤ ዓሣ አጥማጆችም ወደ ወንዝ ሲወርዱና ከወንዙ ሲመለሱ በወንዙም ዳር ሆነው

ከታንኪዎቻቸው አጠገብ ተቀምጠው የእሣ ማጥመጃቸውን መረብ ሲያበጃጁ ዘወትር ይዘፍናሉ። በዚህም ምክኒያት በማሊ ሃገር ይኸ ወንዝ «የዘፋኞች ወንዝ» በመባል ይጠራል። እንግዲያውስ ቃሉ በእርግጥ ከዚህ የመጣ ስለሆነ፣ ናይጀር ማለት የዘፋኞች ወንዝ ማለት እንደሆነ የሃገሩን ቋንቋና የቋንቋንም ስልት የሚያጠኑትን ምሁራን (LINGUISTS) እንዲያጠኑት እንተውላቸዋለን።

ከ ኢ/ ጎርፉ
ሎስ ኤንጀለስ

## የምርምር ሠነዶች፣ ጥያቄዎች፣ ማስታወሻዎች

### ፩ ሥር ነቀል በሆነ መንገድ የወባ በሽታን ስለማጥፋትና በክትባት ስለመከላከል የተደረገ ልምዳዊ ጥናት።

ከዮሐንስ
በስዊድን በኩል
ሚያዝያ 1978 የተዘጋጀ

ይህ ጽሑፍ ልምዳዊ በሆነ ሀገራዊ የአጠናን ዘዴ ተጠንቶ የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ የወባ በሽታንና የመሳሰሉትን በሽታዎች በባህል ሀገራዊ መድሀኒቶች በተለይም በእጽዋት እንዴት ማዳን እንደሚቻል የሚገልጽ ጽሑፍ ነው። አባሪ ሆነው የተላኩትን ሠነዶች ስንመረምር የመድሃኒቅ ፈልሳሚ ከ30 ዓመታት በላይ ሀገራዊ መድሀኒቶች ላይ ጥናት ያደረጉ ከመሆናቸው ሌላ ለወባና ለውሽ በሽታ በተለይ ፍቱን መድሃኒት ማግኘታቸውን (መቀመማቸውን) ተረድተናል። በተጨማሪም ይህ ፈውስ ለብዙሃኑ ሊደረስ የሚችልበትን መንገድ ሲፈልጉ ብዙ ዓመታት አሳልፈዋል። የዓለም ጤና ድርጅቶች ሀሳባቸውን ለመፈፀም አልቻሉም። እንደነዚህ ዓይነት ግኝቶች ለሕዝቡ ጥቅም በአፋጣኝ የሚውሉበት መንገድ መኖሩ እጅግ ጠቃሚ ነው። ሕዝቡ የራሱ ፈላስፋዎች አዋቂዎች ቀጥተኛ ተጠቃሚ የሚሆንበት መንገድና ዋስትና እጅግ አስፈላጊ ነው። ስለሆነም ደራሲው-ሐኪም በሕዝቡ እርዳታ መድሀኒቱን አባዝተው ለሕዝብ ጥቅም እንዲያውሉ የሚረዳ ዘዴ ቢዘየድ ራስን ወደመቻል አቅጣጫ የሚመራን ትክክለኛ መንገድ ነው እንላለን።

ከዚህ ቀጥሎ ከረጅሙ የሐኪሙ/ደራሲ ሪፖርት ባጭሩ እንጠቅሳለን።

ከአዘጋጅው ክፍል፣

ወባ በብዙ የዓለም ክፍሎች በሰፊው ተሰራጭቶ የሚገኝ አሰቃቂ በሽታ ነው። የሚገኝበት አካባቢም ከመሬት መቀነት/ኢኳቶር/ በላቲትዩድ 45 ሰሜን እና 45 ደቡብ ዲግሪ በሚገኘው ስፋት መካከል ነው። በኢትዮጵያ ወባ በማናቸውም የውሀ

ክምችት በቋሚነት በሚገኝባቸው በታዎች ሁሉ የሚገኝ ተሳላፊ በሽታ ነው። እንዲሁም ኢትዮጵያ አልፎ አልፎ የወረርሽኝና ቸነፈር በሽታ የሚያጠቃት ሀገር ናት። የዚህ የወባ በሽታ ሁናቴ በዓመት ውስጥ ከሚያዝያ እስከ ሰኔና ከመስከረም እስከ ኅዳር ባሉት በተወሰኑ ወራት ወቅቱን እየጠበቀ በሽታው ያለማቋረጥ ሕዝቡን ሲያጠቃ እንደኖረ ይታወቃል። የወባ በሽታ ከወረርሽኝና ከቸነፈር በሽታዎች ጋር በመቀላቀል ብዙ ጊዜ ይከሰታል። በተለያዩ ወቅቶች ወባ ገንኖ በሚገኝባቸው በቆላማና ልዩ ልዩ ወባማ ሥፍራዎች አከባቢ የሚገኙትን ሕዝቦች በሽታው ጭርስ ያደርጋቸዋል። የወባ በሽታ ቆላና ወይና ደጋ በሆኑ ሥፍራዎች ከሁለት ሺህ ሜትር /2,000 ሜትር/ በታች በሆኑ ዝቅተኛ አከባቢዎች የሚገኝ በሽታ ነው። በዚሁ በሽታ ምክንያት እነዚህ አከባቢዎች ብዙ ሠፋሪዎች አይገኙባቸውም።

የወባ በሽታ ከሚያስተላልፉ የተለያዩ የፕላስሞዲያ ዓይነት ቢኖርም፣ በዘመናዊ ሳይንስ ተጠንተው የታውቁ አራት ዓይነት ረቂቅ የሆኑ «ፕላስሞዲያ-ፕ.ፋልሲፖሩም፣ ፕ.ቫይቫክስ፣ ፕ.ማላሪያ እና ፕ.ኦቫሊ» የሚባሉ ብቻ በሰው የወባ በሽታ የሚያስተላልፉ ተጠቅሰው ይገኛሉ። የወባን በሽታ የሚያስተላልፉ ሌሎች ዓይነት ትንኞችም አሉ። ሆኖም ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ ዓይነት በአነስተኛ እንስሶች ላይ በሽታውን እንደሚያዘምቱ ይታወቃል።

በኢትዮጵያ ይኸው በቢምቢ ወይም ትንኝ የሚተላለፈው በሽታ በአጠቃላይ የወባ በሽታ በመባል ይታወቃል። ወባ በኢትዮጵያ የሚያጠቃቸው አከባቢና በዝርያቸው የበሽታው ልዩነትና ዓይነት የአድራጎታቸው ስም ይዘው የሚገኙ ጉልተው የሚታወቁ ብዛታቸው እስከ አሥር የወባ ዓይነት ይደርሳል። እነርሱም በኢትዮጵያ ስያሜአቸው እንደሚከተለው ነው።

ንዳድ ፣ ወባ ፣ ሕማመግብጥ/ብጫ ወባ ንዳድ/፣ ሸዋ ወባ፣ ቸነፈር ወባ ፣ እበር ወባ ፣ ብድብድ ወባ ፣ ፈፀንት ወባ፣ ፈራ ወባና ዠማ ወባ ናቸው።

በወረርሽን ገብተው እንደተስበዎች ጥቂት ጥቂት የሚመስሰሉ በመጠኑ የመለያ ድርጊታቸው የሚያስታውቁ ቢኖሩም በኢትዮጵያውያን ቀደምት አዋቂዎች የተጠኑ አጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ሲሆኑ፣ አንድ መደበኛ የወባ በሽታ ሆነው፣ እንደእየሩ አከባቢ፣ እንደየበታው አቀማመጥ ወይም የመነሽ ወራታቸው ወቅቶች ጠባይ ይዘው ይገኛሉ። በእነዚህ በተለያዩ የወባ በሽታ አስተለለፊዎች የሚይዘው በሽታ በተለያዩ ጊዜ ቢከሰትም ብዙ ተመሳሰይነት ይታይበቸዋል።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በወረርሽኝ ወቅት ከሚታዩትና ከፍ ያለ የጤና ችግር ከሚፈጥሩ ዋና ዋና ተላላፊ በሽታዎች የተቅማጥ በሽታና ቅማል ወለድ የተስቦ በሽታ ስለሚገኙበት እዚህ ላይ መጥቀስ የሚያስፈልግ ነው። ባለፉት ዘመናትና በቅርቡ የተገኙት መረጃዎች እንደሚገልጹትም ይኸው የተስቦ በሽታ በኢትዮጵያ በየጊዜው በወረርሽኝ መልክ ከፍተኛ የጤንነት ጠንቅ የሚያመጣ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል። አሁን ባለንበት ዘመን ቢሆንም እነዚህ በሽታዎች የወባ በሽታ ወረርሽኝና ቸነፈር በተከሰተበት ወቅት ጐን ለጐን እንደሚገኙና ብዙውን ጊዜም ተነጣጥለው እንደማይታዩ ከለፉት ልምዶች ሊታወቅ ተችሏል።

ኢትዮጵያ ከሌሎች ብዙ የዓለም ሀገሮች መከከል የተስቦ ተላላፊ በሽታና የግርሽ ትኩሳት በሽታ ከሚያጠቃቸው አንዷ እንደሆነችና በተለይ በደጋው ክፍል በየጊዜው ተስቦ እየተነሳ ችግር እንደሚፈጥርባቸው በዓለም የሕክምና ስነ-ጽሑፎች ውስጥ ተጠቅሶ እናገኘዋለን። ወቅቱም በቀዝቃዛ የክረምት ወራት ቢሆን፣ ወረርሽኝ ከፍተኛ ደረጃ የሚደረስበት በወራቱ መጨረሻ አከባቢ ነው። የወባና የተስቦ በሽታዎች በሁለቱ መከከል በበሽታው ጠባይ ተመሳሰይነት ያላቸው ቢመስሉም፣ የወባን በሽታ ለመለየት የሚያስችሉ ጉልህ የሆኑ ጠባዮች ይታዩበታል። በዚህ ሁኔታም በወረርሽኝ ወቅት ሁለቱም ተላላፊ በሽታዎች ጐን ለጐን ይገኛሉ ቢባልም ከላይ እንደተጠቀሰው ቀደምት ኢትዮጵያውያን የወባን ጠባዮችና ዓይነቶች

በዝርዝር ለማወቅና ለመመደብ ችለዋል።

በአሁኑ ዘመን ለወባ ሕመም መፈወሽ የሚያገለግሉ የተለያዩ መድኃኒቶች በዓይነትና በብዛት መኖራቸውና መገኘታቸው ይታወቃል። ከወባ መድኃኒቶች ሁሉ በተለይ ክሎሮኪን የተባለው እንክብል/ክኒን/ ሰውን የወባ በሽታ ሊያስይዙ የሚችሉት አራት የወባ በሽታ ዓይነቶችን በሙሉ በመፈወስ ብልጫ ስላለዩ፣ ይኸው መድኃኒት ከሌሎቹ የወባ መድኃኒቶች ይበልጥ ይመረጣል። ነገር ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፋልሴፖሩም ማለራያ ለተባለው ከበድ የወባ በሽታ የእንክብሉ/የክኒኑ/ መከላከያ ኃይሉ መቀነሱን የሚገልጹ ሪፖርቶች ከደቡብ አሜሪካ፣ ከደቡብ ምሥራቅ እስያና ከደቡብ ፓስፊክ አካባቢ መድረሳቸው ተገልጿል። እንዲሁም በቅርቡ የዚሁ እንክብል ለፋልሲፓሩም ማለሪያ ያለው የመከላከያ ኃይሉ የቀነሰ መሆኑን ከምሥራቅ አፍሪቃ እንደተደረሰበት ለመታወቅ ተችሏል።

በኢትዮጵያ ያለ የወባ ሕክምና ልምድ አሠራር ለጊዜያዊ መከላከያ ብቻ የሚረዳ ነው። ይህም ማለት ማናቸውም ሰው ወባማ ወደሆኑ ቦታዎች በሚሄድበት ጊዜ ለአንድ ሳምንት ያህል የሚያገለግል አንድ ወይም ሁለት የወባ መከላከያ እንክብል በመውሰድ ይጠቀማል። በእንዲህ ዓይነቱ አጥቃቀም ሰው በወባማው ቦታ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ እንዲሁም ወባ ወደሌለበት አካባቢ ከተመለሰ እስከ ጥቂት ቀናት ድረስ የወባውን እንክብል መውሰድ ይኖርበታል። የወባ መከላከያ መድኀኒት አጠቃቀም በዚሁ ዓይነት መንገድ ሲሆን፣ ሥር ነቀል ፈዋሽ የሆነ የወባ በሽታ መድኃኒት ግን እስከሁን ድረስ ፈጽሞ ያልተገኘለት መሆኑ ይታወቃል።

ለወባ በሽታ ያገኘሁት የባህል መድኃኒት ከሌሎች የወባ በሽታ መድኃኒቶች ጋር ሲነጻጸር መድኀኒትነቱ ፍቱን የሆነ ነው። ምክንያቱም ረቂቆች ሕዋሳትን በፍጥነት ለማጥፋት ችሎታ ስላለው፣ እንዲሁም በጭስ ወይም በሲጋራ መልክ ተዘጋጅቶ በአወሳሰድ በቀላል መንገድ መጠቀም ስለሚቻል ነው። የወባን በሽታ በጭስ መፈወስ በታመመው ሰው ላይ ከፍ ያለ የጤና ቀውስ ተፈጥሮ

የነበረውን፣ ቢጭር ጊዜ ውስጥ ከማናቸውም የወበ ዓይነት በሽታዎች እንዲድን ያደርጋል። የመፈወሱ ሁኔታም እስከ 95% ፍቱን ስመሆኑ በተግበር ለማረጋገጥ ችያለሁ።

በተለያዩ ክፍለ ዓለማት የሚገኙ ወበማ ክፍሎች ለፋልሲፓሩም የወበ በሽታ የተዘጋጀውን የመከለከያ ኃይሉ በመቀነሱ ምክንያት ችግር ተፈጥሮአል። ምናልባትም ይህ ሁኔታ ፍቱን የሆነ የወበ በሽታ መከለከያ መድኀኒት ተገኝቶ በሥራ ላይ የማዋሉ ሁኔታ ገና ብዙ ጊዜ እንደሚዘገይ ሆኖ ይታያል። በተጨማሪም የወበ በሽታ በጉበት ሕዋሰት አከባቢ በሚኖርበት ጊዜና እንደተውሰኩ አይነትም አልፎ አልፎ እያገረሹ በሽተኞችን እንደሚያሰቃዩ ሲታወቅ ምንም ዓይነት ፈዋሽ መድኀኒት አልተገኘለትም ማለት ነው። ይሁን እንጂ የወበ በሽታ ዋና የኅብረተሰብ የጤና ችግር የሚፈጥር ተለላፊ በሽታ በመሆኑ ፈጽሞ ለማጥፋት እንዲቻል ለማድረግ፣ ከለይ በተጠቀሰው ደረጃ ማለት በሽታው በጉበት ሕዋሰት አከባቢ ሳለ ሊያጠፋ የሚችል መድኀኒት መገኘት አለበት። እንግዲያውስ ደግሜ ለማረጋገጥ የምፈልገው የዚህ ሪፖርቴም ዋና ዓላማና የማስተለልፈውም መልእክት ይህ ያገኘሁት/ግኝቴ/ የወበ የበሕል መድኀኒት በእንክብል መልክ በማዘጋጀት ባጭር ጊዜ ውስጥ በጉበት ሴሎች አከባቢ ያሉትን ሕዋሰት (ከሽመቁበት) ቀስቅሰና ገፋፍቶ ተውሰከችን በማጥፋት ሥር ነቀል በሆነ መንገድ የወበ በሽታን ፈጽሞ ለማጥፋት እንደሚቻል ደርሼበታለሁ።

ከዚህ የሕክምና ደረጃ በኋላ ማለት በጉበትና በጣፊያ ሕዋሰት አከባቢ ያሉትን ተውሰከች ፈጽሞ ከጠፋ በኋላ፣ በውበ በሽታ ተለክፎ የነበረ በሽተኛ መከተብ ይኖርበታል። ለክትባት የምጠቀምበት መደበኛ መድኀኒት በዚህ ሪፖርት ከተጠቀሱት ከሌሎች መድኀኒቶቼ ለየት ያለ ራሱን የቻለ ነው። ለወበዎች፣ ለተስበና ለተላላፊ በሽታዎች ይህን መደበኛ መድኀኒት ብቻውን ሌላ ሳይቀለቀልበት ለክትባት ይውለል። የዚሁ የክትባት መድኀኒት አጠቃቀም ከዘመናዊ የሕክምና አሠራር ጋር ሲያነጻጽሩት ልዩነቱ ጉልቶ የሚታየው፣ የክትባቱ መድኀኒት በአንድ መደበኛ መድኀኒት

የሚመራ ሆኖ ለብዙ በሽታዎች ክትባት ፍቱን የመከላከያ ዘዴ ሆኖ ተገኝቷል።

ከዚህ በላይ ስለአነሳሁት ስለክትባት የሚከተለውን ሃሳብ ደፍሬ ከሙሉ እምነት ጋር ለክልበት እወዳለሁ። ይህን እኔ ያገኘሁት የወባ የክትባተ መድኀኒት በመውሰድ ተጨማሪ ጥናት ተደርጉለትና ታክሎበት፣ ደረጃውና ጥራቱ ከፍ እንዲልና እንዲጠበቅ ሆኖ፣ ያለምንም ጥርጣሬ የወባን ቫክሲን በጭር ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ሊዘጋጅ እንደሚቻል እተማመናለሁ። በዚሁ እርምጃ ከተወሰደ በኀላም በዚሁ ቫክሲን በቅርብ ጊዜ ውስጥ በሰው ላይ ሙከራ ተደርጉ ጥሩ ውጤት እንደሚያስገኝ በማመን ለማየት በተስፋ እጠባበቃለሁ።

ልምዳዊ የሆነው የባሕል መድኀኒት ደረጃ በደረጃ የተጤነው ወደፊት ዘመናዊ በሆኑት የፋርማከሎጂ ተቋሞች ውስጥ ይመረታል በሚል እምነት ነው። ይህም በሲጋራ መልክና በእንክብል መልክ ሊሆን ይችላል። ይኸው መድኀኒት መሠረቱ አንድ ሲሆን ተከላከይነትና ሥር-ነቀል በሕርይ ሊኖረው ይችላል። ይህንንም ወደ ኪሚዮቴራፒክ ደረጃ ለማሸጋገር ብዙ ልፋት አያስፈልገውም ብዬ እገምታለሁ። ይህ እንዲህ ከሆነም ይህ ግኝት የዘመናችን ዋነኛ የኬሚካል ግኝት ነው በመባል ሊመዘገብ እንደሚችል ተስፋ አደርጋለሁ።

* * *

የምርምር ሰነዶች...

## ፱ «እንኪን መሞት ማርጀት አለ።»

አበቶች ሲተርቱ «እንኪን መሞት ማርጀት አለ» ይላሉ። ይህን አነጋገር በተለምዶ ለሚጠቀምበት ሰው ወይንም ሞትን በመጥፎነት ለሚመለከተው ታዛቢ፤ አበቶች ሁለቱን የሰው እድገት ተቃራኒዎችን ያለአገባብ በማመዛዘን ተችተዋል ብለው ሒስ ሊያቀርብ ይችላል።

ነገር ግን ሐሳቡንና የሚሰጠውን ትምህርት ለበስ ይዘት አጥልቆ ለሚመለከተው ሰው እውነትን የተመረከዘ ሊታሰብበትም የሚገባ ጥቅስ ነው።

ይህን ጥቅስ (ተረት) ተጠቅሜ በዚህ ጽሑፍ ላይ ሐሳቤን እንዳከፍል ከገፋፉኝ ዋናው ምክንያት፤ በአካባቢየም ሆነ አልፎ አልፎ የማገኛቸውን ኢትዮጵያውያንን (በእድሜያቸው ጠና ያሉትን) በማነጋግርበት ጊዜ እርጅናን በጥላቻ መልክ አብስም በሰሜን አሜሪካ ውስጥ አርጅቶ የመሞት እቅድ እንደሌላቸው፤ እንዲያውም «አገሬ ገብቼ እሞታለሁ እንጅ'ነርሲንግ ሖም፡' (ያርጌዎች የመጨረሻ እድሚያቸውን ከሚያሳልፉበት መጦሪያ ቦታ) አልሄድም» ሲሉ ይዝታሉ። በተጨማሪም በሐገር ውሥጥም ይሁን ወይንም በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ብዙውን ጊዜ በጽሑፋቸው ላይ ሲያተኩሩ የሚታየው፤ የመንግሥትን ይዘት፤ የሐብትን ማዳበርያ፤ በጠቅላለው የሐገርን ልማትና እድገትን በሚነካ መስመር እንጂ ጤናችሁ ወይንም ጤናችን እንዴት ነው? የሐገር እድገት ከጤና ጥበቃ ጋር እንዴት ይዋኃዳል? በማለት ምንም መድረክ ሲሰጡት አይታይም።

ብዙዎችን ለምሳሌ በሰሜን አሜሪካ ቀደም ሲል ማለትም በኢትዮጵያ የመጠቀ ለውጥ ሳይመጣ በፊት የወጣነው ጉልማሶችና ጠንካራ ሰውነት በሞላ ጉደል መልከም ጤና ኖሮን፤ ተምረን የኑሮ ይዘታችን ለማሻሻልና የርጅና እድገታችንም በሐገር፤ ከዘመድ

አዝማድ ጋር፤ በመደጋገፍ፤ እንደተለመደው ደንብ እናስልፋለን በማለት ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን ይህ ምኞት፤ ምኞት ብቻ ሆኖ ሳይቀር አልቀረም። ለምሳሌ፣ በተለይ በታለለቅ ከተማ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን እንደሚገልጹት፤ ሽማግሎች ወለጆቻቸው ለመጉብኘትም ይሁን ወይንም የሐገርን ይዘት በመሰቀቅ ከልጆቻቸው ጋር አመትም ይሁን ሁለት አመት ሲያሰልፉ እንዳደቹም በሞት ሲለዩዋቸውና የኑሮ ክብድነትን «አልሞት ባይ ተጋዳይ» ሆነው እንዴታገሉ ሲያደርገቸው ይታያል።

ከዚያም አልፎ በጠቅለለ ከነጪ አሜሪከዊ (CAUCASIAN ETHNIC GROUP) ለልሆኑት ሕዝቦች፤ የጤና አገልግሎትም ይሁን ወይንም ሌላ የኑሮን ቀንበር የሚያቃልሉለትን አገልግሎቶች፤ በዘረኝነትም ሆነ በጥላቻ መልክ በመመልከት ገለል ተደርገው ጥቅማቸውን እኩል እንዳይከፈሉ በመደረግ ብዙ ውጣ ውረድ እንሚደርስበቸው የጤና ይዘት ተችዎች ያትታሉ። (ጥቅስ 1 እና 2 )

በአጠቃለይ ምን ይደረግ ብሎ መጠየቅ ስለሚገበ፤ ስምና ወርቅ ሌሎቹም ተመሳሳይ መጽሔቶች እርጅናንም ይሁን ወይንም የጤናን ይዘት በሚመለከቱ እርእሰቶች ላይ በለሙያዎችም ሆነ ወይንም ተቆርቋሪዎች እንዲተቹበቸው የመወያያ መድረክ ለጤናችን በሚሰኝ ርዕስ እንቀጽ ለይ፣ የተለዩ በታ ተሰጥቶት (ትችትም ይሁን ወይንም የትምህርት መሰተፊያ) እንዲሆን ትልቅ ጥረት መደረግ አለበት።

ለምሳሌ ስለጤና ይዘት ሊተችበቸው የሚገቡ እርእሰቶች እንደሚቀጥለው ሊሆኑ ይችላሉ።

1. ከሐገር ፈልሰው የሚመጡ አሮጊቶች፣ ወጣቶች (ትምህርትም ያነሳቸው ሆነ ቋንቋ የማይችሉ) እንዴት አድርገው ነው ጤንነታቸውን የሚጠብቁት የአዕምሮ ሰላምስ ለማግኘት የሚያደርጊቸው ትግሎች ምንድናቸው?
2. አልፎ አልፎ ወጣቶች ራሳቸውንም ሆነ ጊደኞቻቸውን ከጉዳት ላይ ሲያደርሱ ይታያል ይሰማልም። ይህን አሰቃቂ ድርጊት

እንደሚፈጸመው በተለያዩ ስቴትስ (የአሜሪካ ክፍለ ሐገር ወስጥ) መንግሥቱም ሆነ ግለሰብ ምን እርዳታ ይሰጣል?

3. የሕክምና እርዳታ ካልተገኘ ወይንም ዋጋው ከናረ እንዴት ነው እነዚህ ከሐገር የፈለሱ ገንዘብ የሌላቸው የሚያገግሙት?
4. ገንዘብ ኖሮአቸው እንኳን ሐኪም በሚያዩበት ጊዜ የዘረኝነትም ሆነ ማንያሀለኝነት ጠባይ ይዘው በቀና መንገድ በሽታቸውን እንደመረምሩዋቸው የማያስችለውን መሰናክል እንዴት ይወጡታል?

ይህንም የመሰሰሉ ሌሎች እንቀጾች ሊኖሩ ይችላሉ።

## የተጠቀሱ መጻሕፍት፤


1. Leininger, m. 1978.
TRANSCULTURAL NURSING, CONCEPTS; Theories and practices

2. Parenti, D et.al, «Health Statas of Ethiopian Refugees in the United Status» American Journal of Public Health, Vol. 77, No. 12, Dec 1987 P. 1542-1543.


ሰምሰም ፀጋው

## ከአዘጋጆው ክፍል፣

ጤንነትና የሕክምና ሳይንስ ላይ የተመሰረቱ ጥናትና ምርምሮች ማውጣት ከዕቅዳችን አንዱ መሆኑን በቁጥር ፩ ላይ ጠቅሰን ነበር። በዚህ ርዕስ ላይ በየጊዜው ጽሑፍ ለማቅረብ በሙያው አከባቢ ያሉ ምሁራን ጥረትና ፍላጎትን ይጠይቃል። ወ/ሮ ሰምሰም እንደገለጹት በአጠቃላይ የኢትዮጵያውያን ጤንነት ጉዳይ ላይ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ጉዳይ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የጤንነት ችግር በቅርቡ ሆነው ሊያጠኑና ሊመረምሩ የሚችሉት በቦታው ላይ ያሉ የሕክምና ሙያተኞች ናቸው። ሌላው ደግሞ ለብዙ ዓመት በሕክምና ሙያ ተሰማርተው ሕዝባቸውን ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ አሁን ውጭ ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ናቸው። የመጽሔታችን መክፈቻ «--- ዕውቀት ያብብ ዘንድ ያገራችንን ልጆች አስተምር --» እንዳለው ሁሉ በየትም ያሉ የሕክምና ሙያተኞች በዚህ መድረክ እንዲሳተፉ ጥሪ እናደርጋለን።

በዓለም ዙሪያ ስለሚገኙት ኢትዮጵያውያን ጤንነት ችግርና መፍትሔ ጥናት ማድረጉ በጣም ጠቃሚ ነው። በየአህጉሩ የሚገኙ የሕክምና ምሁራን በየአከባቢያቸው ስላለው የጤንነት ሁናቴ ጠለቅ ባለና በተቀነባበረ መልክ ምርምር ቢያካሂዱ ለጠቅላላው የጤና ችግርና መፍትሄው ጥሩ መንደርደሪያ ማግኘት ይቻላል።